# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 074 ኅዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ‹‹ስምምነቱ ዓለም አፍሪካ ላይ ያለውን የተሳሳተ እሳቤ እንዲያርም መልዕክት ያስተላለፈ ነው››

- ዶክተር ዮናስ አዳዬ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላም ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር



ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት አፍሪካውያን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍታት እንደሚችሉ በማሳየት ዓለም ለአህጉሪቱ ያለውን የተሳሳተ እሳቤ ማረም እንዳለበት መልዕክት ያስተላለፈ መሆኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላም ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰርና የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን አባሉ ዶክተር ዮናስ አዳዬ ገለጹ፡፡

ዶክተር ዮናስ አዳዬ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም ሃገራት አፍሪካውያን በራሳቸው ማሰብ እንደማይችሉና ዛሬም ቅኝ ግዛት እንደሚያስፈልጋቸው ያምናሉ፡፡ በአፍሪካ

“ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## የቆቦ ከተማ ሙሉ በሙሉ የመብራት አገልግሎት እንዲያገኝ እየተሰራ ነው

ሞገስ ጸጋዬ



ቆቦ፡- የቆቦ ከተማ ሙሉ በሙሉ የመብራት አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ ጉዳት በደረሰባቸው መስመሮች ላይ የጥገና ስራ እያከናወነ መሆኑን በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የወልድያ ዲስትሪክት የቆቦ አገልግሎት መስጫ ማእከል አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የቆቦ አገልግሎት መስጫ ማእከል ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ወንደሰን ኃይሌ እንደገለጹት፣ በጦርነት ምክንያት እስከ 2014 ጥቅምት ወር መጀመሪያ ድረስ የቆቦን ከተማ ጨምሮ በአካባቢው የመብራት አገልግሎት ተቋርጦ ነበር። ነገር ግን ከወልድያ ዲስትሪክት የተለያዩት ቡድኖችን በፍጥነት በማዋቀር ጉዳት የደረሰባቸውን መስመሮች ጥገና በማድረግ የቆቦ ከተማ የመብራት አገልግሎት ማግኘት ችሏል። ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እየተሰጠ ስላልሆነ ቀሪ ስራዎችን በማጠናቀቅ አገልግሎቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲዳረስ ሌት ተቀን እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

የቆቦ ከተማ ሙሉ በሙሉ የመብራት አገልግሎት እንዲያገኝ ሰራተኞች ቀን ማታ ሳይሉ ከእሁድ እስከ

የቆቦ ከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ሸኔ ሕዝብ እየገደለና እየዘረፈ የራሱን ምቾት ለመጠበቅ የሚንቀሳቀስ ስብስብ ነው”

- አትሌት ፈይሳ ሌሊሳ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ሸኔ ሕዝብን እየገደለና እየዘረፈ የራሱን ምቾት ለመጠበቅ የሚንቀሳቀስ የዘራፊ ስብስብ መሆኑን አትሌት ፈይሳ ሌሊሳ አስታወቀ:: የሕዝቡ ሰቆቃ እንዲያበቃ የሸኔ ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቋጫ እንዲያገኝ በቁርጠኝነት መስራት እንደሚገባም ጠቁሟል:: ሰሞኑን በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል

“ሸኔ ሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የሰላም ስምምነቱ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ እንደግፈዋለን

-የቆቦ ከተማ ነዋሪዎች

ሞገስ ጸጋዬ

ቆቦ፡- በአፍሪካ ህብረት መሪነት በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው ስምምነት ዘላቂነት ያለው ሰላም እንደሀገር ለማረጋገጥ የሚረዳ በመሆኑ እንደሚደግፉት አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡ የቆቦ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ፡፡

የቆቦ ከተማ ነዋሪ አቶ አለሙ ወዳጆ እንደገለጹት፣ በአሁኑ ወቅት በቆቦ ከተማ ሰላም ሰፍኗል፣ አሁን የመጣውን የሰላም ስምምነትም ሕዝቡ በጸጋ ተቀብሎታል። እንደ አገር ሰላም ለመሆን መንግሥት የጀመረው የሰላም ሂደት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባልም ብለዋል።

ሰላም በሀገር ደረጃ በዘላቂነት እስኪረጋገጥ ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን መቆም አለበት ያሉት አስተያየት ሰጭው፤ ከጦርነት የሚገኝ ትርፍ ባለመኖሩ ሰላም እንዲመጣ በጎ አስተዋጽኦ ማድረግ ከህዝቡ ይጠበቃል። የቆቦ ከተማ ህዝብም ሰላም በሀገር ደረጃ እስኪረጋገጥ ከመንግሥት ጎን ይቆማል ብለዋል፡፡

በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት የቆቦ ሕዝብ በጸጋ ይቀበለዋል፣ እውን እንዲሆንም ፍላጎት እንዳለው ጠቁመዋል። እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በማጠናከር ቅራኔንና አላስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ማስወገድ እንደሚገባም ገልጸዋል።

የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








የወይዘሮ ተስፋዬን የኑሮ መሰረት የቀየረው የጓሮ ልማት

ገጽ 3

# አዲሱ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያ የአካባቢውን የኃይል ፍላጎት እንደሚያሟላ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዳማ ከተማ የተገነባው የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የተሻለ አገልግሎት እንዲቀርብ እያደረገና በቀጣይም የአካባቢውን የኃይል ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የትራንስሚሽንና ሰብስቴሽን ግንባታ ፕሮጀክት ስራ አስፈጻሚ ክብሮም ካህሳይ ለጉብኝቱ ተሳታፊ ጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ጣቢያው 250 ሜጋ ዋት ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል ነው።

ጣቢያው በዋናነት ለኢንዱስትሪ ፓርኮች በተሻለ ሁኔታ ኃይል እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑንም ጠቁመው፤ ለፕሮጀክቱ ግንባታ 13 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ተጨማሪ 150 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገ ሲሆን፤ ወጪውን ሙሉ በሙሉ የሸፈነው መንግስት መሆኑን ተናግረዋል።

ከወራት በፊት ስራ የጀመረው ጣቢያው በአሁኑ ወቅት በተሻለ ሁኔታ የኤሌክትሪክ ኃይል እየሰጠ መሆኑን አመልክተው፤ የአዳማንና አካባቢውን ኃይል አቅርቦት በከፍተኛ ደረጃ ማሳደጉንም አስረድተዋል።

በቀጣይም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በጋራ በመሆን አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤የአዳማ ሰብስቴሽን



የተገነባው በከተማዋ እየተስፋፉ ለሚገኘው ኢንዱስትሪዎች እና ለተጠቃሚዎች በቂ የኃይል አቅርቦት ለማሟላት መሆኑን አስታውቀዋል።

ግንባታው በ2008 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን ወደሙሉ የግንባታ ስራው የተገባው ደግሞ በ2011 ዓ.ም እንደሆነ ታውቋል።



አቶ ዮናስ አለማየሁ

# በአዲስ አበባ የልደት ሰርተፊኬትን በጤና ተቋማት መስጠት ተጀመረ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግስትና የግል የጤና ተቋማት የልደት ሰርተፍኬት በነፃ መሰጠት መጀመሩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ አለማየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በሚገኙ የጤና ተቋማት ከዚህ በፊት የልደት ሰርተፍኬት አይሰጥም ነበር። ይህም በሀገሪቷ የሚገኙ ነዋሪዎችን ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ አዳጋች አድርጎታል።

ከዚህም ባለፈ መንግስት በየአመቱ የሚበጅተው በጀት ከተማሪ ምገባ፣ ዩኒፎርምና ለትምህርት ቤቶች የሚያስፈልገው የመምህር ብዛት እንዳይታወቅ አድርጎታል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ምን ያህል ህፃናት እንደተወለዱ፣ ምን ያህል ዜጎች እንደተጋቡና እንደሞቱ መታወቅ አለበት ብለዋል።

ይህን ለማድረግ በከተማዋ በሚገኙ የጤና ተቋማት የልደት ሰርተፍኬት መስጠት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በከተማዋ በሚገኙ የመንግስትና የግል የጤና ተቋማት የልደት ሰርተፍኬት በነፃ በመሰጠት ላይ ይገኛል። በዚህም ቴክኖሎጂን ቀዳሚ አድርገን እየተንቀሳቀስን ነው ብለዋል።


እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ በጤና ተቋማቱ ባለሙያ ተመድቦ ምዝገባ እየተከናወነ ይገኛል። የልደት የምስክር ወረቀቱ በ33 የጤና ተቋማት እየተሰጠ በመሆኑ እናቶች ልጆቻቸውን አስመዝግበው በተወለዱበት ቀን ሰርተፍኬት ይዘው እየሄዱ ነው።

አገልግሎቱ በግል የጤና ተቋማት እየተሰጠ ሲሆን ከመንግስት የጤና ተቋማት ውስጥ ዘውዲቱ፣ ጋንዲ፣ ጴጥሮስና ጳውሎስን የመሳሰሉት ይገኛሉ። እነዚህም አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ ውልደት የሚከሰትባቸው የጤና ተቋማት ናቸው። ይህም እንደ ሀገር የመጀመሪያው መዋቅር ነው ብለዋል።

በጤና ተቋማት የሚሰጠው ምዝገባ ነፃ ነው። አሁን በሚሻሻለው የከተማው አገልግሎት ክፍያ ደንብም የሞትና የወቅታዊ ምዝገባ ክፍያ እንዲሁም የልደት ክፍያ ነፃ ነው። ህፃናት የልደት ሰርተፍኬት አልወሰዱም ማለት በመንግስት አይታወቁም ማለት ነው። ስለዚህ ህፃናት በተወለዱበት ወቅት ተመዝግበው ሰርተፍኬት ሊሰጣቸው ይገባል ብለዋል።

በጤና ተቋማቱ የሚመዘግበው ባለሙያ የሚመራበት የራሱ የሆነ መዋቅር አለው ያሉት አቶ ዮናስ፤ ተቋሙ በከተማዋ የሚወለድ ህፃን ሳይመዘገብ መቅረት የለበትም ብሎ እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

በተቋሙ ለውጥ ሲመጣ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና የልማት ኤጀንሲ የሚፈልጉትን በአንድ ላይ በማሰባሰብ፣ መሰረታዊ የዘርፍ ተነሳሽነትን ለማሳደግና የአገሪቱን ዲጂታል ኢኮኖሚ ጉዞን ለማሳለጥ እንዲሁም የኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በግንባር ቀደምትነት ለመምራት የሚያስችል ሥራ እየተሰራ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡



# የሳይበር ሉዓላዊነትን ስመጠበቅ የባለተሰጥኦዎችን አቅም ማጎልበት ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሳይበር ሉዓላዊነት በዘላቂነት ለመጠበቅ የባለተሰጥኦ ታዳጊዎችን አቅም በማጎልበት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አስታወቀ።

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሳይበር ልማት ማዕከል ኃላፊ አቶ ካሳሁን ደሳለኝ እንደተናገሩት፤ ማዕከሉ አሁን ላይ ለ120 ተሰጥኦ ያላቸው ታዳጊዎች ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡

የማዕከሉ ሰራተኞች ወደ ትምህርት ቤቶች በመሄድ ጭምር ተሰጥኦ ያላቸውን ታዳጊዎች ለይተው ወደ ማዕከሉ እንዲቀላቀሉ እያደረጉ መሆኑንና ወደ ማእከሉ ለሚመጡ ታዳጊዎች የቁሳቁስና የባለሙያ ድጋፍ እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ባለፈው ክረምት ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ከመላው አገሪቱ የተውጣጡ 60 ታዳጊዎች ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉን አንስተው፤ በቀጣይ ይህንን ስራ ለማስፋት ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ስምምነት መፈፀሙን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን የሳይበር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ታዳጊዎች ላይ መሰረት ያደረገ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ታዳጊዎች በድረገፅ cychallenge.insa.gov.et እንዲሁም ወደ ተቋሙ በመምጣት ተመዝግበው ተሰጥኦዋቸውን ማጎልበት እንደሚችሉም ተናግረዋል።

ታዳጊ ሞሂቦን ኢብሳ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን፤ ለሶፍትዌር ፈጠራ ስራ የተለየ ፍቅር እንዳለው አመልክቶ፤የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በመከታተልና መረጃዎችን በማንበብ ህልሙን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱንም ነው የገለጸው፡፡

ለፈጠራ ስራዎች ውጤታማነት የተቋማት እገዛ ወሳኝ ሚና እንዳለው ገልጾ፤ ከዚህ አኳያ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ስር በሚገኘው የሳይበር ታለንት ልማት ማዕከል ባገኘው ድጋፍ የተለያዩ መተግበሪያዎችን መስራት መቻሉን ተናግሯል፡፡

በተለይ የትምህርት ቤት አስተዳደር ስርዓት መተግበሪያው በሚማርበት ትምህርት ቤት ጥቅም ላይ መዋሉን ያነሳው ታዳጊው፤ ማእከሉ ለባለተሰጥኦ ወጣቶች የፈጠራ ስራ ቁሳቁስን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል ብሏል፡፡

በማዕከሉ ያሉ ባለሙያዎች እርሱን ጨምሮ ለታዳጊዎች ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ነው የገለጸው፡፡ በተመሳሳይ የ11ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ዳግም አበበ እና የ12ተኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ለሁሉም ቁምላቸው ወደ ማዕከሉ ከመጡ ወዲህ ለሙያቸው መዳበር የሚሆኑ ስልጠናዎችን እያገኙ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ማእከሉ በተለይ ወጣቶች እርስ በርስ ልምድ እንዲለዋወጡ እድል የፈጠረ መሆኑንም አንስተው በዘርፉ ተሰጥኦ ያላቸው ታዳጊዎችም ወደ ማዕከሉ በመምጣት የኢትዮጵያን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ መጠየቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# “የኢትዮጵያ ጀግኖችን ታሪክ ለትውልዱ በማስተማር ሀገር ወዳድ ዜጋን የማፍራት ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል”

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ጀግኖችን ታሪክ ለትውልዱ በማስተማር ሀገር ወዳድ ዜጋን የማፍራት ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

በመዲናዋ ልደታ ክፍለ ከተማ በአዲስ መልኩ የተገነባው የሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ትምህርት ቤት እና ሐውልት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የአብዲሳ አጋ ቤተሰቦች፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አባላትና ሌሎች እንግዶች በተገኙበት ትናንት ተመርቋል።

ከንቲባ አዳነች እንዳሉት፤ ታሪክ ሰርተው ያለፉ ጀግኖቻችንን በመዘከር እና በማስተማር ትውልድ እንዲገነባበት መስራት ያስፈልጋል። ለዚህም ለሀገር ትልቅ ውለታ ያበረከቱ ጀግኖችን ታሪክ በስርዓተ ትምህርት በማካተት በየትምህርት ቤቶችና ሌሎችም የማስተማሪያ ዘዴዎች ለትውልዱ የማስተማር ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የጀግኖችን አርዓያ በመከተል ለኢትዮጵያ ዕድገት የሚተጋ ሀገር ወዳድ ዜጋን የማፍራት ስራን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ያሉት ከንቲባዋ፤ የከተማ አስተዳደሩም በሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ስም



በ1965 ዓ.ም ተገንብቶ የነበረውን በእርጅና የፈራረሰውን ትምህርት ቤት በአዲስ መልኩ እንዲገነባ ማድረጉን ተናግረዋል።

ከዚህም ባለፈ አብዲሳ አጋን የሚዘክር ሀውልት በማቆም ለትውልዱ የጀግኖችን ታሪክ ለማውረስ መስራቱን ጠቁመዋል። አብዲሳ አጋ በዓለም የታወቀበት የጀግንነት ታሪክ ትውልድን በሀገር ፍቅር ለመገንባት የምንጠቀምበት በመሆኑ እንኮራለን ነው ያሉት።

የሌተናል ኮሎኔል አብዲሳን ታሪክ ስናወሳ ጽናትና ጀግንነትን ለአገር ትልቅ ስራ ሰርቶ ማለፍን ያስተምረናል ብለዋል። የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው፤ ድንበርና እስር ካልገደበው የአብዲሳ አጋ የጀግንነት ታሪክ ተማሪዎች ብዙ እንደሚማሩ ተናግረዋል።

የጀግኖች ታሪክ በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ተካትቶ አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ ትውልዱ እንዲማርበት የማድረጉ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ተወካይ ሻምበል ተድላ ጸጥአርጋቸው በበኩላቸው፤ ከአብዲሳ አጋ ታሪክ ትውልድ እንዲማርበት ከተማ አስተዳደሩ የሰራው ተግባር የሚደነቅ ነው ብለዋል።

ሌተናል ኮሎኔል አብዲሳ ከአገር አልፎ በአውሮፓ ምድር የዘለቀና በጠላት ጭምር የተመሰከረለት ጀግና መሆኑን ተናግረው፤ ከዚህም ባለፈ በጣሊያን እስረኞችን ከእስር በማስለቀቅ እና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በጣሊያን ሮም ያውለበለበ የኢትዮጵያ ጀግና መሆኑን ለትውልድ ማስተማር ይገባል ነው ያሉት።

የሌተናል ኮሌኔል አብዲሳ አጋ ልጅ ወይዘሮ አኒሳ አብዲሳ በበኩላቸው፤ ከተማ አስተዳደሩ ጀግናው በትውልድ ልብ ውስጥ ህያው ሆኖ ታሪኩ እንዲዘከር መታሰቢያ በመቆሙ ምስጋና አቅርበዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

ሌተናል ኮሌኔል አብዲሳ አጋ በወለጋ ነጆ በ1911 ዓ.ም የተወለዱ ሲሆን በ14 ዓመታቸው የክብር ዘበኛን በመቀላቀል ከዚያም ከገነት ጦር ትምህርት ቤት በ50 አለቃ ማዕረግ ተመርቀዋል። ፋሽስት ጣሊያን በ1928 ዓ.ም ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ከሌሎች አርበኞች ጋር ሀገራቸውን ከጠላት ተከላክለዋል፤በተለያዩ ጦር ሜዳዎች ጀብዱ በመስራት በ1970 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።



# ማዕከሉ 100 የተሻሻሉ የወተት ላሞችን ለአርሶአደሮች አከፋፈለ

## - በኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች የሌማት ትሩፋት መርሃግብር ተጀምሯል

**በዳግማዊት ግርማ**

ሆለታ፡- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል በምርምር ያወጣቸውን የተሻሻሉ 100 የወተት ላሞች ዝርያዎችን ለአካባቢው አርሶ አደሮች አከፋፍሏል። በትናንትናው እለት 'የሌማት ትሩፋት' ማስጀመሪያ መርሐ-ግብር በሆለታ ከተማ ተከናውኗል።

የምርምር ማዕከሉ በምርምር ያወጣቸውን የተሻሻሉ 100 የወተት ላሞች ዝርያዎችን ለአካባቢው አርሶ አደሮች ያከፋፈለው ትናንት በሆለታ ከተማ በተካሄደው የክልሉ የሌማት ትሩፋት ማስጀመሪያ መርሃግብር ላይ ሲሆን፤ ላሞቹ ከፍተኛ መጠን ያለው የወተት ምርት መስጠት የሚችሉ እንደሆኑና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሮቹ መሰጠታቸውም ተመላክቷል።

በሌማት ትሩፋት መርሀግብር ማስጀመሪያው ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ባስተላለፉት መልዕክትም ኢትዮጵያን መቀየር የሚቻለው ግብርናን መቀየር ሲቻል ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ከሰማንያ በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝቧ ህይወቱን በግብርና ስራ ላይ ላደረገችው ኢትዮጵያ ትልቅ የኢኮኖሚ እድገት ከተፈለገ የግብርናውን ዘርፍ ቅድሚያ በመስጠት መስራት እንደሚያስፈልግ ነው ፕሬዚዳንቱ የገለፁት።

የሌማት ትሩፋት ንቅናቄው እንዲሳካ የክልሉ መንግስት ምርጥ ዘርን፣ ሌሎች የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን አሟጦ መጠቀም ይገባዋል ሲሉ ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አሳስበዋል፡፡

የመኖ አቅርቦትን ማሻሻል እንዲሁም የእንስሳት ጤንነትን መጠበቅ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጠው የጠቆሙት አቶ ሽመልስ፤ በየጊዜው በግብርና ዘርፍ ለተሰሩ ስራዎች የዘርፉን ተዋንያን እንዲሁም አርሶአደሮችን አመስግነዋል።

በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በበኩላቸው፤ ኦሮሚያ እንኳን ለኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሌማት ትሩፋት መስጠት የምትችል ለምለም ምድር ባለቤት ናት ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኃይለማርያም ገለፃ፤ ስፍራውን በጥናት በተደገፈ ስራ ከኢትዮጵያ አልፎ አፍሪካን የሚያጠግብ ማድረግ ይቻላል።

በሌማት ትሩፋት መርሀግብሩ ኦሮሚያን እንቁላልና ዶሮ ለበዓላት ብቻ ሳይሆን በአዘቦትም የሚትረፈረፍባት ለማድረግ የሚያስችል ስራ እየተከናወነ መሆኑንም አቶ ኃይለማርያም ገልፀዋል።

የግብርና ዘርፍ ባለሙያዎች፣ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ ጠንክረው ከሰሩ አገሪቷ ከዚህ ንቅናቄ ብዙ ታተርፋለችም ሲሉ ነው አቶ ኃይለማርያም የገለፁት።

ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፈረስ እንዲሁም የሆለታ ከተማና ህዝብ የክብር ጋቢ በስጦታነት ሰጥተዋቸዋል።

ከመርሐ-ግብሩ ጎን ለጎን በሆለታ ግብርና ምርምር ስር የተቋቋመው የዶሮ እርባታ ምርምር ማዕከል ተመርቆ ተከፍቷል። የምርምር ማዕከሉ ሦስት ሺህ የዶሮ ጫጩቶች ይዞ ስራ የጀመረ ሲሆን ዶሮዎችን ለአካባቢው አርሶ አደሮች እንደሚያሰራጭም ተገልጿል።

በተያያዘ ዜና በደቡብ ክልል በሌማት ትሩፋት መርሐግብር የወተት፣ የማርና የስጋ ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታውቋል፡፡ በክልሉ የሌማት ትሩፋት የንቅናቄ መድረክ በሀላባ ቁሊቶ ከተማ እየተካሄደ መሆኑንም ኢዜአ ዘግቧል።

በደቡብ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ ኡስማን ሱሩር እንዳሉት፤ በሌማት ትሩፋት የወተት፣ የዶሮ፣ የማርና የስጋ ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ ነው።

የሌማ ትሩፋቱ ከእንስሳት ሃብት ልማት፣ ከስራስር እና ከእንሰት ተክል ጋር ተሳስሮ እንደሚተገበር የጠቆሙት ኃላፊው፤ የእንስሳት ዝርያን ለማሻሻል የሚደረገው ጥረት የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብሩን ስኬታማ ለማድረግ እንደሚያስችልም ጠቁመዋል።

በእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ስራ እስከ 35 ሊትር ወተት የሚሰጡ ላሞች ማግኘት እንደተቻለም ጠቁመዋል።

በክልሉ 3 ነጥብ 1 ሚሊዮን የወተት ላሞች እንደሚገኙና ከዚህ ውስጥ 93 በመቶ የሚሆኑት የሀገረሰብ ዝርያ መሆናቸውን ገልጸው፤ የወተት ምርት ከነበረበት ሁለት ሊትር በአማካይ 14 ሊትር ለማድረስ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ የዶሮ ዝርያንም በማሻሻል ከአንድ ዶሮ በአመት እየተገኘ ያለውን 50 እንቁላል ወደ 280 ለማሳደግ እንሰራለን ብለዋል።

በንቅናቄ መድረኩ ላይ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳውን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ተሳትፈዋል።

የሌማት ትሩፋት ዘመቻ በአገር አቀፍ ደረጃ በአርባምንጭ ከተማ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይፋ መደረጉ ይታወሳል።

# የወይዘሮ ተስፋዬን የኑሮ መሰረት የቀየረው የጓሮ ልማት

**አዲሱ ገረመው**

"ጎራ ብላችሁ ቤት ያፈራውን መመገብ አለባችሁ" አሉን በእንግዳ ተቀባይ ለስላሳ ድምጽ:: የኢትዮጵያዊነት ስሜት ዘልቆ የገባው የገጠር ሰው ሁሌም እንዲሁ ነው:: የእንግዳ ተቀባይነታቸው ሥርዓት ከቤታቸው ጎራ እንድንል አስገደደን::

ለስላሳ በሆነ አንደበታቸው ምን ይጨመር እያሉ፤ ብሩካን በሆኑ እጆቻቸው ወጡን እየጨለፉ በአይኖቻቸው በስስት እየተመለከቱን ለሥራ የሄድነውን ሁሉ መግበው አጠገቡ:: በሌማቱ የቀረበልን ትኩስ ምግብ ለወትሮው ወዝ አልባ የሆነውን ቆዳዬን በላቦት ነከረው:: ምክንያቱ ደግሞ ሁሉም የጓሮ በረከት መሆኑ ነው::

ወይዘሮ ተስፋዬ የዓለም ይባላሉ:: በምዕራብ ጎጃም ዞን ሰሜን አቸፈር ደንተባ በተሰኘ አነስተኛ መንደር ነዋሪ ናቸው:: ከእጃቸው የበላነው የጓሮ ሌማት ጣእሙ ቢያስገርመን ከህይወታቸው ጨልፈው እንዲያጫውቱን ማውጋት ጀመርን::

እኒህ የአምስት ልጆች እናት ከባለቤታቸው ጋር በመሆን በሚያመርቱት የጥራጥሬ እህል ለዓመታት ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ህይወት ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ መቆየታቸውን ይናገራሉ:: ሆኖም ይህ ለኑሯቸው በቂ ባለመሆኑ ቤተሰቦቻቸው ችግር ላይ ወድቀው እንደነበር ያስታውሳሉ እንስቷ፤ የኑሮ ጫናን ለማቃለል በራሳቸው አቅም ከወሰዱት መፍትሄዎች አንዱ የጓሮ ልማትን ማስፋፋት ነበር:: በዚህም አበረታች ውጤት ማግኘተቻውን ይገልጻሉ::

የውሃና መሬት ሀብት ማዕከል የመማሪያ ተፋሰስ ፕሮጀክት ባደረገላቸው ድጋፍ የዛሬ ሁለት ዓመት ነው ሥራውን የጀመሩት:: በዚህች ሥፍራ ላይ ተፈጥሮን ያማከለ እንዲሁም የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊጠቅም የሚችል የፍራፍሬና አትክልት ልማት ሲጀምሩ ይህ እንዴት ውጤት ሊኖረው ይቻላል? ተብልን ነበር ይላሉ:: የሰው አፍ ፈተና ሆኖ ብዙ ሳያደክማቸው ሥራውን ሙጥኝ ማለታቸውን አልተውም::

የተነሳሽነታቸውና ቁርጠኝነታቸው ተግባር አካባቢውን በማልማት፣ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ በመቀየርና ምርትን በማብዛት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተም ነው ወይዘሮዋ የሚናገሩት::

በጀመሩት የጓሮ ልማት የጓሮ አትክልትን አዘውትሮ መመገብ ለጤና የሰጣቸው ጠቀሜታ ሰፊ እንደሆነ፤ ምርታቸውን ለገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ መሆናቸውን፤ ልጆቻቸውን እንደ ልብ ማስተማር መቻላቸውን ያብራራሉ:: ገበያ ላይ ገዝተው ከመመገብ ይልቅ በጓሯቸው የተተከሉትን ትኩስና ጤናማ ተክሎች አዘውትረው በመመገባቸው የተሻለ የጤና ጠቀሜታ ማግኘታቸውን



ይገልጻሉ:: ሌሎች እንስቶችም የእርሳቸውን ፈለግ ተከትለው ጓሮአቸውን በማልማት ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዲያገኙ ይመክራሉ::

የቁንዝላን መስመር ይዞ ከኮሮኮንች እየተጋፋ የሚጓዘው ተሽከርካሪያችን በምእራብ ጐጃም ዞን ሳንክራ ቀበሌ ነዋሪ ወደሆኑት ወይዘሮ በጽሀ አስማረ ቤት አድርሶናል:: ወይዘሮዋ በእድሜ ጠና ቢሉም እርጅና ለሚጫጫነው ድካም እጅ አልሰጡም:: ልክ እንደ ወይዘሮ ፍትፍቴ እርሳቸውም የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬን በማልማት ለአካባቢው ምሳሌ መሆን የቻሉ ናቸው።

ያሏቸውን የጓሮ ቦታዎች ተጠቅመው ከአትክልት ድንች፣ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ካሮት፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ ቃሪያ ከፍራፍሬ ደግሞ አቡካዶ፣ ፓፓያ፣ ብርቱካንን በመትከል ተጠቃሚ መሆናቸውን ይናገራሉ::

በአካባቢው የጓሮ ልማትን ከሚተገብሩት እንስቶች መካከል አንዷ የሆኑት ወይዘሮ በጽሐ፤ በሠሩት ልማት በአካባቢው ውበቱ የተጠበቀ ገጽታ እንዲሁም ነፋሻማ አየር እንዲኖር አድርገዋል:: የጓሮ አትክልት ልማቱ በምግብ እጦት እንዳይቸገሩ ትልቅ ፋይዳ እንደሰጣቸው ያብራራሉ::

ከትዳር አጋራቸው ጋር ተመሳሳይ ህልም ያላቸው ወይዘ በጽሐ፤ ለገበሬው ትልቅ የእውቀት ማዕከል የሆነውን በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ በጎ ተጽእኖ ማሳረፍ የቻለውን ልማት አልምታው አርዓያ መሆን የቻሉበትን “የአረንጓዴ ድንኳን” የአትክልት ማፍሪያ ቦታን ተክለው ለገበያ በማቅረብ ጭምር ተጠቃሚ መሆናቸውን ይናገራሉ::

ጠባቧን ጓሮ እንዴት እንደ ሺህ ሄክታር ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል አይተናል:: ያውም ቀምሰን:: ሰርቶ ማሳየት ብቻ ሳይሆን በሚጣፍጥ ሙያ ሰርቶ ማብላትን ተግባራዊ ያደረጉ እንስቶች እዚህም እዚያም ሽማምቶ ሳይሆን በጓሮ ላይ ከዘሯቸው አትክልቶች አማርጠው መመገብ መቻላቸው እንደ አገር የተጀመረውን ምግብን ከጓሮ ንቅናቄ የሚያበረታታ መሆኑ ልብ ይሏል::

## ‹‹ስምምነቱ ዓለም አፍሪካ ላይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ህብረት መሪነት የተፈረመው የሰላም ስምምነት ዓለም ለአህጉሪቱ ያለውን የተሳሳተ እሳቤ ማረም እንዳለበት መልዕክት ያስተላለፈ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በሰላም ስምምነቱ የታየውን የአፍሪካውያን የመፍትሔ ባለቤትነት በሌሎችም መስኮች መድገም እንደሚገባ ጠቁመው፤ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኘውን ሰፊ እርሻ በማዘመን ኢኮኖሚውን ማሳደግና የጤና ችግራችንን ለመቅረፍም የባህል መድሃኒቶቻችን ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት የአህጉሪቱ ቀጣይ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

ፓን አፍሪካኒዝምን ማጎልበትና እንደ አህጉር የነጻ ገበያ ስርዓትን ማጠናከር፣ ቀጣናዊ ትስስር የበለጠ እንዲጠናከር ማድረግ በአጭር ጊዜ ለውጥ ለማምጣት እንደሚያግዝ ጠቅሰው፤ በሁሉም መስክ ነጻነትን በማረጋገጥ ዛሬም ድረስ ትእዛዝ ከምዕራባውያን ዓለም መጥቶ በአፍሪካ ምድር እንዲፈጸም የሚፈልጉ አካላትን ህልም ማምከን እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በተለይ በወጣቶች ዘንድ የአፍሪካዊነት ስሜት እንዲያድግ አፍሪካዊ አንድነትን የሚያጎለብቱና ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎችን የሚያመላክቱ ትምህርቶችን ቀርጾ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን አመልክተው፤ የመገናኛ ብዙሃንም አፍሪካዊነትንና የአፍሪካ ችግሮች በአፍሪካውያን መፈታት የሚችሉ መሆናቸውን በደንብ በማስተጋባት ሚናቸውን መወጣት አለባቸው ብለዋል፡፡

የሰው ልጅ መገኛ፣ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ምንጭ የነበረችውን አፍሪካ እንደገና ለመላው ዓለም ማሳየትና አፍሪካን መናቅ አቁመው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤትም ተገቢው መቀመጫ እንዲሰጣት አበክሮ መሥራት እንዳለበትም ዶክተር ዮናስ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

«የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ» በሚለው ብሂል መሰረት ራስን ማድነቅ እንደሚገባ የጠቆሙት ዶክተር ዮናስ፤ የምንማራቸው ትምህርቶች በሙሉ ችግር ፈቺና የቅኝ ግዛት አስተሳሰብን ከአዕምሯችን ጭምር ማስወገድ የሚያስችሉ እንዲሆኑ በትኩረት መሥራት ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

ለአፍሪካውያን አንድነት መጠናከር የኢትዮጵያ ሚና የማይተካ መሆኑን አስታውሰው፤ በአህጉር ደረጃ ትልቅ ዋጋ የሚሰጠውን ይህን ስምምነት ወደ መሬት እንዲወርድ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ከመንግሥት ጎን ተሰልፈው የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## የቆቦ ከተማ ሙሉ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እሁድ እየሰሩ ነው ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ ጉዳት የደረሰበት መስመር ከአላማጣ እስከ ቆቦና በራያ ቆቦ ወረዳ ሳተላይት ጣቢያዎች ጭምር ናቸው። ከአላማጣ እስከ ቆቦ ያለው የከፍተኛ መስመር የመጠጥ ውሃ የያዘውን መስመር ጨምሮ አምስት የሚሆኑ ቡድኖችን በማሳተፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በአሁኑ ጊዜ የቆቦ ከተማ ሰማንያ በመቶ የኤሌክትሪክ ኃይል አግኝቷል ያሉት አቶ ወንደሰን፤ ቀሪውን ሃያ በመቶ አጠናቆ ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ ነው። በራያ ቆቦ ስር የሚተዳደሩ ሳተላይት ጣቢያዎችን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ አንድ ቡድን በማሰማራት ስራዎችን እየሰራን እንገኛለን። እስካሁንም ገደመዩ፣ አዲስ ቀኝ፣ አማያ፣ አዋሬ የተባሉ የገጠር ከተሞችም የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በዞብል የኮንክሪት ፖል ተከላዎች አልቀዋል ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ በቀጣይ የሽቦ መሳብ ስራ በመስራት የመብራት ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል። የአካባቢው ማኅበረሰብ ለአንድ ዓመት ከአራት ወር መብራት ተጠቃሚ አልነበረም፣ የመልሶ ጥገና በማከናወን የኤሌክትሪክ አገልግሎት በማግኘቱ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶታል። ጥገናው በፍጥነት እንዲጠናቀቅ የአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

የጦርነት ቀጣና ሆኖ በመቆየቱ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል የሚሉት አቶ ወንደሰን፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ለመስጠት ጉዳት የደረሰባቸውን ምሰሶዎች በአዳዲስ እየቀየርን ነው ሲሉ ገልጸዋል።



አቶ ተገኝ አሰፋ



አቶ አስሙ ወዳጆ



ወይዘሮ ሙሃባ ነጋሽ



ወጣት አለ በየነ

## የሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለሰላም ድርድር ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄዱ ሲባል የቆቦ ሕዝብ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶታል ያሉት ወይዘሮ ሙሃባ ነጋሽ በበኩላቸው፤ ለሰው ልጅ ሰላም አስፈላጊ በመሆኑ አሁን በተደረሰው የሰላም ስምምነት ተደስተናል፣ እውን እንዲሆንም ሁላችንም የበኩላችንን ሚና መጫወት ይኖርብናል ብለዋል።

ጦርነት አስከፊ ከመሆኑም በላይ ድህነትንና ችግርን ይዞ የሚመጣ በመሆኑ የሰላም ሂደቱ ሊደገፍ ይገባል። እውን እንዲሆንም ሁሉም ከመንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል። ቀጣይ አገር ተረካቢው ወጣት በመሆኑ በስምምነቱ ተደስቷል፡፡ ይህንን የሰላም ሂደት ለመደገፍም ዝግጁ ናቸው ብለዋል። የትግራይ ሕዝብና የአማራ ሕዝብ እርስ በርስ የተዋለደ በመሆኑ ያለው አማራጭ ተስማምቶ መኖር መሆኑን ወይዘሮ ሙሃባ ገልጸዋል።

የቆቦ ከተማ ነዋሪ የሆነው ወጣት አለ በየነ በበኩሉ፤ የቆቦ ከተማ ወጣቶች አጥብቀው ሰላም ይሻሉ። በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ለወጣቱ ተስፋ ሰጥቷል። ከምንም በላይ ደግሞ ከመንግሥት ጎን በመሆን ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ እስኪረጋገጥ እንዲሁም በልማቱ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት እንዲጠናከሩ እንሠራለን ብሏል።

ሰላም የማይሹ በጦርነት ሲጠቀሙ የነበሩ አንዳንድ ሀገር አፍራሾች መኖራቸውን ያነሳው ወጣቱ፤ የሰላም ስምምነት የለም እያሉ የሕዝቡን አስተሳሰብ ለመበረዝ ሙከራ እያደረጉ በመሆኑ መንግሥት በፍጥነት ሰላሙ እውን እንዲሆን ሊሰራ ይገባል ብሏል፡፡ የቆቦ ሕዝብ እንደ ሕዝብ ከመንግሥት የወረደ አቅጣጫን ይቀበላል፣ ስምምነቱም ወጤት እያመጣ ነው። በቀጣይ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ገልጿል።

አሁን የመጣውን የሰላም ስምምነት ሕዝቡ ሊንከባከበው ይገባል ያሉት ሌላኛው የቆቦ ከተማ ነዋሪ አቶ ተገኝ አሰፋ፣ ሰላም ካልመጣ የውጭ ጣልቃ ገብነት ይባባሳል፣ ይህም ልማትን ያቀጭጫል። እንዲሁም አንድነትን ሳይሆን ልዩነትን ያባብሳል ብለዋል። ስምምነቱ ለሕዝቡ ተስፋ ሰጥቷል፣ የተሰደደው ወደ ቀየው እየተመለሰ ነው። ስምምነቱ በፍጥነት ወደ መሬት እንዲወርድ ሁሉም ወገኖች በቁርጠኛነት ሊሰሩበት ይገባል ብለዋል፡፡

የፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት በአፍሪካ ህብረት አመቻችነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ለ10 ቀናት የሰላም ንግግር ካካሄዱ በኋላ ጥቅምት 23 ቀን 2015 ዓ.ም የሰላም ስምምነት መፈራረማቸው ይታወሳል።

የሀገር መከላከያ ሠራዊትና የሕወሓት ታጣቂዎች አመራሮችም በኬንያ ናይሮቢ የሰላም ስምምነቱን የማስፈጸሚያ እቅድና የሕወሓት ታጣቂዎች የትጥቅ አፈታት ሂደት ላይ ህዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም መስማማታቸው ይታወሳል።

ስምምነቱ ህገ መንግሥታዊ ስርዓቱን ያከበረ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ያስጠበቀ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ሊኖር የሚገባው አንድ የመከላከያ ሠራዊት ብቻ መሆኑን የሚያጸና ሲሆን፤ የስምምነቱን መርሆዎች ተግባራዊ ለማድረግም ሕወሓት ትጥቅ ሊፈታ፣ ታጣቂዎቹም ወደ ተሃድሶ እንዲገቡ ከስምምነት መደረሱ ይታወሳል፡፡

በስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው መሰረት መንግሥት በግጭቱ የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም ከዓለም አቀፍ አጋር አካላት ጋር በፍጥነት ወደተግባር ገብቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

## “ሸኔ ሕዝብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት በተያዘው ዕቅድ መሰረት ወደግቡ ከደረሰ ትልቅ ስኬት ነውም ብሏል።

አትሌቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ እንደ ሀገር ሸኔ በህዝብ ላይ ያደረሰው ተጽእኖ ከባድ ቢሆንም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ በተለይ በኦሮሞ አርሶ አደር ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ለመናገር እንኳ የሚከብድ ዘግናኝ ተግባር ነው።

ቀደም ሲል የቡድኑ እንቅስቃሴ እና ግፉ በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ነበረ ያለው አትሌት ፈይሳ፤ አሁን ላይ ግን ግፉም እንቅስቃሴውም በጣም ስለጨመረ ለጉዳዩ ተገቢ ትኩረት ካልተሰጠ መዘዙ ከአሁኑ የከፋ ይሆናል ብሏል።

ለአገሪቱ ሰላምና ለሕዝቡ እፎይታ እስከ ሆነ ድረስ ከሸኔ ጋር በሰላማዊ መንገድ በመነጋገር መረጋጋት ከሰፈነ መነጋገር መልካም ነበር። ይሁንና ቡድኑን የሚመራ አካል በውል በማይታወቅበትና የትግሉም ዓላማ ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ ሰላማዊ መንገድ መፍትሄ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም ብሏል።

በተጨማሪም ሰውን በማገት በአንዴ በርካታ ብሮችን እጁ የሚያስገባና የሽፍታነት ባህሪ ያጎለበተ ታጣቂ በድርድር ወደ መደበኛ ኑሮ ይመለሳል ብሎም ማሰብ እንደሚከብደው የተናገረው አትሌት ፈይሳ፤ ከዚህ አንጻር ምናልባት የተወሰኑትን ወደ ሰላም ማምጣት ከተቻለ ቀሪው ላይ የኃይል ርምጃ ማጠናከር እንደሚቻል አስገንዝቧል።

እንደ አትሌት ፈይሳ ማብራሪያ፣ በመጀመሪያው አካባቢ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ሕዝቡን ከቡድኑ ጋር የመፈረጅ አዝማሚያዎች ነበሩ። በሌላ በኩል ደግሞ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ሆነውም ከሸኔ ጋር የሚሰሩ አካላት አሉ።

በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ አመለካከቶች ሸኔን መስመር ለማስያዝ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ውስብስብ እንደሚያደርጉት የጠቆመው አትሌቱ፤ ከዚህ አንጻር ሸኔን ለመዋጋት ባለው ጠንካራ አቋም ምክንያት በአንዳንድ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ባሉ አካላት ጥላቻና ጫና

እንደሚደርስበትም አልሸሸገም። በተጨማሪም ቡድኑ ላይ የሚደረገው ኦፕሬሽን በተወሰነ መልኩ ቁርጠኝነት እንደሚጎድለውም ጠቁሟል።

ቀደም ሲል እሱ ባለበት አካባቢ ሲንቀሳቀስ የነበረውን የኦነግ ሰራዊትም ሆነ አሁን ያለውን የሸኔ ቡድን እንደሚያውቃቸው የተናገረው አትሌት ፈይሳ፤ ነባሩ የኦነግ ሰራዊት ቅጠላቅጠልና ሥራሥር እየበላ ለዓላማው ከመንቀሳቀስ ውጪ ሕዝቡን አስቸግሮ እንደማያውቅ ጠቁሟል። ሆኖም አሁን ያለው የሸኔ ቡድን አባላት ሕዝብን እየገደለና እየዘረፈ የራሱን ምቾት ለመጠበቅ የሚንቀሳቀስ የዘራፊ ስብስቦች ነው ሲል በንጽጽር ገልጿል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት የሚደነቅ ነው ያለው አትሌት ፈይሳ፤ ነገር ግን ያ ሁሉ ሕይወት ከመጥፋቱ፣ ንብረት ከመውደሙና ብዙ ዋጋ ከመከፈሉ በፊት ቢሆን ብዙ ችግሮችን መቅረፍ ይቻል እንደነበርም ጠቁሟል።የስምምነቱን ተግባራዊነትና ዘላቂነት ማስጠበቅ ቀጣዩ ትኩረት መሆን እንዳለበትም አሳስቧል።

“ሰይጣን ካልሆነ ሰላም የሚጠላ ሰው አይኖርም” ያለው አትሌት ፈይሳ፤ ሸኔም ቢሆን ለሰላም ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ከያዘው መስመር ቢወጣ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነው፤ ነገር ግን ሕዝቡ ከዚህ በላይ በዚህ ቡድን መቸገር የለበትም፤ ችግሩን ለመፍታት በቁርጠኝነት መስራት ይገባል ብሏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መንግስት የጀመረው የሰብአዊ ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥል!

በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ኢትዮጵያ ያሸነፈችበት፤ አፍሪካም የውስጥ ችግሮቿን በራሷ አቅም መፍታት እንደምትችል ያሳየችበት፤ ኢትዮጵያውያንም ለሰላም ሲሉ ሁሉንም ዋጋ ለመክፈል ያላቸውን ቁርጠኝነት ያረጋገጡበት ነው:: ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያን ሉዓለዊነቷንና የግዛት አንድነቷን ያጸና፤ አንድነቷን ያስጠበቀ፤ ለመላው ኢትዮጵያውያን በተለይም በጦርነት ቀጣና ውስጥ ለነበሩትን የትግራይ፣ የአማራና የአፋር ክልል ህዝቦች እፎይታን አጎናጽፏል::

ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በአንድ ልብ ወደልማትና ብልጽግና እንዲያተኩሩም ምቹ ሁኔታንም ፈጥሯል:: ጉዳት የደረሰባቸው አከባቢዎችን መልሶ ለመገንባት፣ የሰብዓዊ ድጋፍንም ያለገደን ተደራሽ ለማድረግም እድል የሰጠ ሲሆን፤ ከስምምነቱ ማግስት በመንግስት በኩል ለተፈጻሚነቱ እየወሰዳቸው ርምጃዎችና እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ደግሞ የመንግስትን የሰላም ቁርጠኝነት የገለጡ ናቸው::

በዚህ ረገድ ከዚህም ከፕሪቶሪያው ስምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው:: በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብአዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መደላድል የሆነ፤ በትግራይና በአማራና በአፋር ክልሎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፣ የኤሌትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎች እንዲከናወኑ፤ የጥገና ስራዎቹ በተጠናቀቁባቸው አከባቢዎችም አገልግሎቶቹ እንዲጀምሩ ያስቻለም ሆኗል::

በተለይ ሰብዓዊ ድጋፍን ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከስምምነቱ ማግስት ጀምሮ መንግስት ኮሚቴ በማቋቋም ወደስራ ገብቷል:: ለአብነትም ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ሰብአዊ ድጋፍ የጫኑ 67 ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ ገብተዋል:: ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሽሬ፣ ሽራሮና አክሱም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ፣ የመድሃኒት እና የሕክምና ቁሳቁስ ድጋፎችን ማዳረስ ችለዋል::

ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበርም ወደ ሽሬ የሙከራ በረራ ማድረጉንና ርዳታ በአየርም በየብስም ለማድረስ እየሰራ መሆኑን መግለጹ አይዘነጋም። ካሳለፍነው ሳምንት ጀምሮም ማኅበሩ በትግራይ በዘጠኝ የህክምና ተቋማት መድሃኒቶችንና አስቸኳይ ዕርዳታዎችን በማከፋፋል ላይ ይገኛል:: ዩኒሴፍም ከስምምነቱ ወዲህ ወደ ትግራይ የመጀመሪያው ህይወት አድን ድጋፍ በተለይም ለህፃናት እና ሴቶች አስገብቷል::

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በግጭት የተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር አካባቢዎች የሰብአዊ ድጋፍ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በመንግስትና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በመከናወን ላይ ይገኛል:: በተለይ መንግስት የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት መሰረት በማድረግ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በቁርጠኝነትና በተሟላ መልኩ እየተወጣ ሲሆን፤ በአጋር አካላት በኩልም ማቅረብ በቻሉት መጠን የሰብአዊ እርዳታና መድሃኒት በሁሉም አቅጣጫ ወደ ትግራይ ክልል እንዲያስገቡ እያደረገ ይገኛል::

ይህ የመንግስት ተጨባጭ ጥረትና ፍላጎት ታዲያ በሌላኛው ወገንም በስምምነቱ መርህ መሰረት ይበልጥ ወደ ተግባር መቀየር ይገባዋል:: የወደሙ መሰረተ ልማቶችን እንደገና መገንባትና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ እንዲሁም የሰብአዊ ድጋፎችን ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ማድረስ የፕሪቶርያውም ሆነ የናይሮቢው ስምምነት አካል እንደመሆናቸው መጠን የስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖችም ሆኑ ሌሎች አጋር አካላት ለተግባራዊነታቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል::

በተለይም በመንግስም ሆነ በሌሎች ግብረሰናይ ድርጅቶች የሚቀርቡ ሰብዓዊ ድጋፎች ለተጎጂ ወገኖች መድረሳቸውን ማረጋገጥ የሁሉንም ተሳትፎ ይጠይቃል:: ከዚሁ ጎን ለጎንም ከከተሞች ርቀው የሚገኙ ወገኖች በሎጅስቲክ እጥረት ምክንያት ርዳታው ሳይደርሳቸው እንዳይቀር ክትትል ማድረግና ምቹ ሁኔታ መፍጠርም ይገባል::

በአጠቃላይ በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ እና በኬንያ ናይሮቢ የተካሄደው የሰላም ስምምነት ፍሬ እያፈራ መሆኑን እየቀረቡ ካሉ ሰብአዊ ድጋፎችና የመልሶ ልማት ግንባታ ስራዎች መረዳት ይቻላል:: ሆኖም እነዚህ ጅምር የመንግስት ጥረቶች እስከ መጨረሻው እንዲዘልቁና በጦርነቱ የተጎዱትን የትግራይ፤ የአማራና አፋር ክልል ህዝቦች ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ሁሉም አካላት በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል:: በአንጻሩ የሰላም ስምምነቱ መርሆዎች ወደ ተጨባጭ ተግባር እንዳይቀየር እንቅፋት የሚፈጥሩ ኃይሎች ካልተገባ እንቅስቃሴያቸው ሊታቀቡ ይገባል:: በመሆኑም የተጀመረውን የሰላም ሂደት ዘላቂነት ማረጋገጥ፤ በመንግስት የተጀመሩ የሰብዓዊ ድጋፍና መልሶ ግንባታ ተግባራትን የበለጠ ማጠናከር ከሁሉም ወገኖች ቁርጠኝነት ሊሰራ የሚገባው ነው::


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ባዮ-ቴክኖሎጂ እና ግብርና...

ግርማ መንግሥቴ

በሁለቱ መካከል ስላለውም ሆነ ስለሚኖረው ትስስር ከውዝግብ ባለፈ አንድ ድምዳሜ ላይ አልተደረሰም። በጉዳዩ ላይ ቢያንስ ሁለት ጎራዎች ሊታረቅ እንኳን የማይችል በሚመስል መልኩ ሲፋለሙ ነው የሚታየው፤ የሚሰማውም ንትርክ እንደዛው ነው። አንደኛው ጎራ "በአሁኑ ዘመን ያለ ባዮቴክኖሎጂ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት መጠበቅ የዋህነት ነው" ሲል፣ ሌላኛው ጎራ በበኩሉ ይህንን አስተሳሰብ ራሱን "የዋህነት" ይለዋል። ምክንያቱንም "ባዮቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ውጤታማ መሆን በሰው ልጅ ሕይወትና ጤና ላይ መቀለድ ነው" ሲል ያቀርባል። ይህ አይነቱ ውዝግብ በአንድ ጋዜጣና ጋዜጠኛ የሚፈታ ባለመሆኑ ጉዳዩን ለባለ ሙያዎቹ ትተን እየሆነ፣ እየተደረገ ባለው ላይ እንነጋገር። አስቀድመን ግን የፅንሰ ሀሳቡን ባለቤትና ዘመን እንግለፅ፤ ውለታም ነውና እናስታውሳቸው።

"ባዮቴክኖሎጂ" የሚለው ፅንሰ ሀሳብ በ1919 ኤሬኪ (Ereky, Karl) የተባሉ ተመራማሪ ሀንጋሪ ውስጥ ባዘጋጁትና በርሊን አሳትመው በብዙ ሺህ ኮፒዎች በተቸበቸበውና በ1921 ወደ ደች ቋንቋ በተተረጎመው፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በጉዳዩ ላይ ባተኮረው መጽሐፋቸው አማካኝነት ለአደባባይ የበቃና ወደ ተግባርም የገባ ነው:: ጸሐፊውም አብዮት አስነስተሃል ተብለው ለእስር የተዳረጉ፣ እዛው እስር ቤትም እያሉ (ከ12 ዓመታት የእስር ቆይታ በኋላ) ጁን 17 ቀን 1952፣ በ74 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ለመግቢያ ይህል ይሄን ካልን ዘንድ ወደ ጉዳያችን እንመለስ።

በአሁኑ ዘመን እየተከናወነ ያለው የግብርናው ዘርፍ እንቅስቃሴ በበርካታ ዘርፎች እየተደገፈ ሲከናወን ነው የሚታየው። የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመንና ውጤታማ ለመሆን እንደ ድሮው ማረሻና ሞፈር ብቻ በቂ ሆነው አልተገኙም። ይህ በተለይ ባደጉት ሀገራት የሚታሰብ አይደለምና ሙሉ ለሙሉ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ግብርና ነው እየተካሄደ ያለው። ከእነዚህም አንዱ አምስት ሰፋፊ ዘርፎች (ሰብዓዊ፣ አካባቢያዊ፣ ኢንዱስትሪያዊ፤ እንዲሁም እንስሳትን እና እፅዋትን የተመለከቱ) ያሉት ባዮቴክኖሎጂ ነው።

ይህ ሳይንሳዊ የምርምር ዘርፍ በግብርናው መስክ ሥራ ላይ የማዋል ጉዳይ ዘፈቀዳዊ ሳይሆን ታስቦበትና አስፈላጊው ደንብና መመሪያ ተዘጋጅቶለት የሚተገበር ነው:: ከእነዚህም መካከል አንዱ ዘርፉ ለሚገለገልባቸው ሙያዊ መዝገበ ቃላት ሳይቀር የተዘጋጀለት መሆኑ ነው:: ለዚህም የአሜሪካውያኑን Agricultural Biotechnology Glossary በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

ከ1970ዎቹ ጀምሮ በፍጥነት እየገሰገሰና በስፋት ሥራ ላይ እየዋለ ባለባት ሕንድ ከታች እስከ ላይኛው የትምህርት ተቋም ድረስ በትምህርትና ጥናት መስክነት ይሰጣል:: የውጭ ተማሪዎችም በአገሪቱ ነፃ የትምህርት እድል እየተጠቀሙ ዘርፉን በማጥናት በ"ስፔሻላይዜሽን" ይመረቁበታል። ጉዳዩ እዚህ እንደምንፅፈው ቀላል አይደለምና፤ እያንዳንዱን ሰው፣ እንስሳ፣ እፅዋት፣ አዝርዕት፣ አካባቢ ... ይመለከታልና እኛም አገር ወደ ፊት በኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና መሰል ተቋማት አማካኝነት ብዙ ይሠራል ብለን እንጠብቃለን።

ባደጉት ሀገራት ባዮቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ከዋለ ትንሽ ሰንበት ያለ ሲሆን፣ አፍሪካን በመሳሰሉና በማደግ ላይ ባሉ አገራት ቴክኖሎጂው ገና በመግባትና በትውውቅ ደረጃ ላይ ይገኛል። ትንሽ ቀደም ባሉትና ቴክኖሎጂውን ተግባራዊ ባደረጉ ታዳጊ አገራት ላይ ግን ውጤት እየታየ ነው እየተባለ ሲሆን፣ ሁሉም ሀገራት ይህንኑ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ካሉባቸው ዘርፈ ብዙ ችግሮች ሊላቀቁ ይገባል የሚለው ምክረ ሀሳብ እያየለ በመምጣት ላይ ነው።

ከእነዚህ አገራት መካከል አንዷ ሀገራችን ስትሆን፤ ቴክኖሎጂውን በትውውቅ ደረጃ ከመጠቀም አልፋ ወደ እለት ተእለት ተግባራት ውስጥ ያስገባችው ይመስላል። ለዚህ ማሳያው ደግሞ በ"የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን" አማካኝነት ተዘጋጅተው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቀውና (BIODIVERSITY REGULATORY LEGAL FRAMWORKS OF ETHIOPIA, Addis Ababa 2022 በሚል ርዕስ) በአንድ ተሰንደው በOFAB Ethiopia (Open Forum on Agricultural Biotechnology) አማካኝነት ለባለ ድርሻ አካላት የተሰራጩት ፖሊሲዎች፣ ደንብና መመሪያዎች ናቸው።

ሰነዶቹ በሁለት ቋንቋዎች (አማርኛና እንግሊዝኛ) የተዘጋጁ ሲሆን፣ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን (በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች፣ ባለ ሀብቶች፣ ተጠቃሚዎች፣ አገልግሎት ሰጪዎች ... ወዘተ) ያስተናገዱ፤ ስለ ጉዳዩ ግንዛቤን የሚያስጨብጡና በዘርፉ ለሚሠማራ አካል በራስ የመተማመን አቅምን የሚፈጥሩ ስለ መሆናቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲነገሩ ይሰማል።

በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶችም ሆኑ የዓይንና የብእር ምስክሮች እንደሚያስረዱት አፍሪካን ለመሳሰሉና በከፋ ድህነት ውስጥ የሚኖሩ፤ በከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር እየተጥለቀለቁና የእለት ጉርስ ለቸገራቸው፤ ነገር ግን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብትና እሴት ለተሞሉ አህጉራት ባዮቴክኖሎጂን የመጠቀም ጉዳይ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። በልቶ ማደር ካስፈለገ፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ካስፈለገ፣ ምርትን ለውጪ ገበያ ማቅረብና ምንዛሪን ማስገባት ካስፈለገ፣ የአገርን ጂዲፒ ማሳደግ ካስፈለገ .... ካስፈለገ ... በግብርናው ዘርፍ ባዮቴክኖሎጂን መጠቀም የግድ እንጂ ለድርድር የሚቀርብ፤ "እንደ አስፈላጊነቱ ..." የሚባል ጉዳይ አይደለም።

ከላይ በጠቀስነው የሀገራችን ሰነድም ላይ የሰፈረው የሚነግረን ይህንኑ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ባዮቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ኃይሉ ዳዲ (ዶ/ር) በአንድ ወቅት ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ባደረጉት ቆይታ የሚያሰምሩበት ይህንኑ ነው።

ከላይ የጠቀስነው የአሜሪካው መዝገበ ቃላት የግብርና ባዮቴክኖሎጂን A range of tools, including traditional breeding techniques, that alter living organisms, or parts of organisms, to make or modify products; improve plants or animals; or develop microorganisms for specific agricultural uses. Modern biotechnology today includes the tools of genetic engineering. በማለት የሚበይነው ሲሆን፤ ይህ ብያኔም በተለያዩ መንገዶች ከላይ በጠቀስነው የአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ስብስብ ሰነድ ውስጥም ተጠቅሶ ይገኛል። genetic engineering የሚለው "ዘረ መል" መሆኑ በማብራሪያ ተደግፎ፤ የአሠራር ብያኔ ተቀምጦለት ቀርቧል።

ወደ አፍሪካ እንመለስ፤ በአሁኑ ሰዓት ባዮቴክኖሎጂ በአፍሪካ በከፍተኛ ደረጃ ሥራ ላይ ውሎ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። አገራትም ይህንኑ ቴክኖሎጂ እየተጠቀሙ በከፍተኛ ደረጃ እየተለወጡ እንደሚገኙ እየተነገረና እራሳቸውም ምስክርነትን እየሰጡ ይገኛሉ፤ ኢትዮጵያም አንዷ ናት። ምርታማነታቸው ከመጨመሩ የተነሳም ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ሀገራትም እየተረፉ እንደሚገኙም እየተናገሩ ይገኛሉ። ምርታቸውን እየላኩ ዶላሮችን እያስገቡ መሆናቸውም እንደዛው።

ሲጠቃለል፤ "አዝርዕትን፣ እንስሳትን፣ እንስትን፣... የማላመድና ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ሥራ በ.... ተካሄደ/ተከናወነ ..." ከሚለው ባለፈ ኅብረተሰቡ፣ ቢያንስ በጠቅላላ እውቀት ደረጃ የተወሰነ ግንዛቤ ይኖረው ዘንድ ሊሠራ ይገባል። በሂደቱ ተሳታፊም ተጠቃሚም ይሆን ዘንድ አስቀድሞ የጋራ ግንዛቤ ሊኖረው ያስፈልጋልና ባልተቋረጠ መልኩ ሊሠራ ይገባል።

ከላይ ሀገራትን የጠቀስነውም ይህንኑ ልምዳቸውን ለማሳየት ነውና እኛም ወደ'ዛው ልናመራ የግድ ነው። ይህንን ስንል ያለ ምክንያት ሳይሆን በተጠቃሚውም ሆነ አጠቃላይ ማኅበረሰቡ ዘንድ፣ ከአያያዝና አጠቃቀም (safety considerations የሚባለውን ጨምሮ) ያለው ግንዛቤ በቂ ነው የሚባልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ቀርቶ ጭራሹንም ስለ መኖሩ የሚያሳዩ ምልክቶች ባለመኖራቸው ነውና ሊታሰብበት ይገባል።

# ተጠየቅ

# «ሕገወጥነትን በሚያበረታታ ድርጊት ላይ ሲሳተፉ የነበሩ የባንክ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለዋል»

**- አቶ ብሴን ጊዜወርቅ**
**የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፤ የአገሪቱ የፋይናንስ ፍሰት በአግባቡ እንዲሳለጥና እክሎች እንዳያጋጥሙት፤ ችግሮች ካጋጠሙም በፍጥነት በማረም በሕግና ደንብ የሚመራ የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖር ይሠራል።በዋናነት ደግሞ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይንም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ጥቅም ላይ እንዳይውል፤ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ እንዲሁም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ብዜት በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን የመከላከል፣ መቆጣጠርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን ይወጣል።

የዝግጅት ክፍላችንም የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት አሁናዊ ተልዕኮዎች፣ ቀጣይ ውጥኖች፣ እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባራትና የመሳሰሉትን በተመለከተ ከፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሴን ጊዜወርቅ ጋር ቃለመጠይቅ አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋነኛ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**አቶ ብሴን፡-** የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት መስሪያ ቤት 490/2014 በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መልሶ የተቋቋመ ተቋም ነው።ተልዕኮውም በወሳኝነት በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይንም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ እንዲሁም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ብዜት በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን የመከላከል፣ መቆጣጠርና ባለድርሻ አካላትን የማስተባበር ብሎም ዓለም አቀፍ ግዴታዎችን መወጣትን ያካትታል።ወንጀሎቹ ድንበር ተሻጋሪና ዓለም አቀፍ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ ሥርዓት አለ።በዚህ ውስጥ የምንወጣው ሚና አለ፤ ይህን በተመለከተ አገራዊ ውክልና ወስደን እንሠራለን።

በቀጥታ ከወንጀሎች ጋር በተያዘዘ ከተለያዩ ሪፖርት አድራጊ አካላት ጋር በተለይም የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ካልሆኑ ተቋማት ሪፖርት ማድረግ ካለባቸው አካላት እንዲሁም ከኅብረተሰቡ በምናገኛቸው መረጃዎች ላይ ተመስርተን መረጃዎችን የመተንተን ሥራዎችን እናከናውናለን።ተንትኖ የወንጀል ፍሬን የመለየት እንዲሁም በሕግ የተያዙትን ጉዳዮች ለሕግ አስከባሪ የማስተላለፍ ሚና አለው።

ይህን ስናካሂድ በመሠረቱ «መኒ ላውንደሪንግ» ላይ ብናተኩርም ለዚህ አመንጪ የሆኑ ወንጀሎችንም ጭምር በትኩረት እናያለን።ከዚህ አንጻር አገራዊ የስጋት ተጋላጭነት ጥናት መሠረት በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ አመንጪ ተብለው የተለዩት ሙስና፣ ኮንትሮባንድ፣ ግብር ማጭበርበር፣ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርንና የመሳሰሉ የወንጀል እንዲሁም ሌሎች ፋይናንስ ነክ የሆኑ ማጭበርበር ተግባራትን እንደ አመንጪ ወንጀል በመውሰድ፣ ትንታኔ በማድረግና የወንጀል ፍሬዎችን በመለየት ለሕግ አስከባሪ አካላት ለተጨማሪ ምርመራና ክስ የምናስተላልፍበት ሁኔታ አለ።እነዚህ በወሳኝነት የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋነኛ ተግባራት ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይንም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ እንዲሁም የጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎችን ብዜት በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎች ምን ያክል ለኢትዮጵያ ስጋት ናቸው?**

**አቶ ብሴን፡-** እነዚህን ወንጀሎች በአግባቡ መከታተልና መቆጣጠር እስካልተቻለ ድረስ በአገር አቀፍ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ሥጋት ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።ኅብረተሰቡ ላይ በቀጥታ ጉዳት የሚያስከትሉ፣ አገር የሚጎዱ፣ በፍትሃዊነት ሠርቶ መበልፀግ ሳይሆን በሕገወጥ መንገድ መጠቀም ለሚሹ አካላት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ነው።እንዲሁም ጤናማ ከሆነው የኢኮኖሚ ውድድር ውጪ በአቋራጭ ለመክበር ለሚፈልጉ አካላት ጥሩ ሁኔታ ይፈጥራል።

አልፎ አልፎም ለአገራት የሠላምና መረጋጋት ችግር የሚሆንበትና በሕገ ወጥ መንገድ ገንዘብ ያከማቹ አካላት



ግጭትን በገንዘብ ይደግፋሉ።በአጠቃላይ የአንድን አገር ዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት የሚያዛባ፣ ሠላማዊ ኑሮና የመንግሥትን ሥርዓት የሚያውክ፣ ማህበራዊ ሕይወትን የሚያዛባና ለሌሎች ሕገ ወጥ ድርጊቶችም የሚዳርግ ነው።መንግሥት ለሕዝብ ተገቢውን አገልግሎት እንዳይሰጥ የሚያደርጉና የመንግሥትን ሥርዓት የሚያዳክሙ አገርን የሚያናጉና ለሠላም እጦት መንስዔ ሊሆኑ የሚችሉ አደጋዎች ናቸው።ስለዚህን እነዚህን በአግባቡ መቆጣጠርና መከታተል ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በተጨባጭ በአገራችን የሚታዩ በርካታ ግጭቶች፣ ኮንትሮባንድ ንግድ፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር አሉ። ይህ ሁኔታ በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ትንተና እንዴት ይታያል?**

**አቶ ብሴን፡-** ሕገ-ወጥነት ሁልጊዜም የሚኖር ነው።በአንድ አገር ወይንም ማህበረሰብ ውስጥ የሚስተዋል ሲሆን ይህን የሚመርጡ አካላት ደግሞ ሕገወጦች ናቸው።በተለይ ደግሞ በሕጋዊ ንግድ ውድድርና ባበረከቱት አስተዋፅኦ ከማደግ ይልቅ በአቋራጭ ለመክበር እንደ ትልቅ አጋጣሚ የሚጠቀሙበት አካሄድ ነው።እነዚህ አካላት ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሉ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ።

ከዚህ አንፃር የሕግ ክፍተቶችን የሚጠቀሙ ሲሆን፣ በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ያሉትን አካላት ጭምር በማሳሳት ይህን ተግባራቸውን ያሳካሉ።ስለዚህ እንደ እሳቤ በአቋራጭ የመክበርና ፍላጎት ነው ብሎ ቢወሰደም እነዚህ አካላት በዚህ የሚቆሙ ሳይሆን ከዚህ ያለፈ ፖለቲካዊ ፍላጎት ይኖራቸዋል።በተለይ ደግሞ አገር ከተረጋጋ እና ሠላማዊ ከሆነ የእነዚህ አካላት ምቹ ሁኔታ እየጠበቡ ስለሚሄዱ ሁሌም አገር ባልተረጋጋ ሁኔታ እንዲኖር ይሠራሉ።የተለያዩ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ስለሚኖራቸውና ይህን ለማሳካት ደግሞ ከፍተኛ ገንዘብ ፈሰስ ያደርጋሉ፤ ወደሚፈልጉት ይረጫሉ።ይህ አካሄድ በአገር ውስጥ ብቻ የሚገደብ ሳይሆን እስከ ውጪ ድረስ ትስስራቸውን የሚዘረጉበት አጋጣሚና አግባብ አለ።

እንደ ማሳያ ብንወስድ ውጭ አገር ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ለቤተሰቦቻቸውና ለተለያየ ዓላማ ወደ አገር ውስጥ ገንዘብ ይልካሉ።ታዲያ ሕገ-ወጦች የሚያደርጉት በሕጋዊ መንገድ ወይንም በባንክ ሥርዓት መምጣት ያለበትን ወደ አገር ውስጥ መግባት ያለበትን ገንዘብ ወይንም የውጭ ምንዛሪ እዚያው ውጭ በጥቁር ገበያ ላይ ግዥ በመፈፀም ገንዘቡ ወደ አገር ውስጥ እንዳይገባ በማድረግ በአገራቸው ላይ ትልቅ ወንጀል ይፈጽማሉ።እነዚህ ግለሰቦች በዚህ መልኩ ውጭ ያስቀሩትን ገንዘብ ለሌላ አላማ ሊያውሉት ይችላሉ።አንደኛ በሕገ ወጥ ንግድ ምርት አገር ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ።በተጨማሪም ደግሞ አገር ውስጥ በሕገ ወጥ ያከማቹትን ለማሸሽ ይጠቀሙበታል።

**አዲስ ዘመን፡- ከፍተኛ አመራሮችና ሕገ ወጦች ወዳጅነት ፈጥረው የሚሠሩበት አጋጣሚ መኖሩን ገልፀውልኛል። ይህን ሁኔታ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት በተጨባጭ ደርሶበታል?**

**አቶ ብሴን፡-** እንግዲህ የምናደርጋቸው ኦፕሬሽናልና ስትራቴጂክ የትንተና ሥራዎች በእያንዳንዱ ኬዝ ውስጥ የሚሳተፉ አካላትና ግለሰቦችን የመለየት ሥራ አብሮ ይሠራል።በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚችሉ አካላትና ግለሰቦችን እንደየድርሻቸው የመለየት ሥራ ይሠራል።ምክንያቱ ደግሞ የሕግ ተጠያቂነቱም እንደተሳትፎም መሆን ስላለበት ያንን ተግባር እናከናውናለን።

በዚህ ሂደት ውስጥ በግል ወይንም በንግድ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነገር ግን ሕገ-ወጥ ተግባር የሚፈጽሙ አካላት የሚገኙበት ሁኔታ አለ፤ እንዲሁም በመንግሥት ሥራ ላይ ሆነው ኃላፊም ይሁን ባለሙያ የዚህ ድርጊት ደጋፊ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ።በዚህ አግባብ እነዚህም አካላት አንዱ የሕግ ተጠያቂነት ሊያርፍባቸው ስለሚገባና ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ስላለባቸው ይህን የሚመለከት መንግሥት አካል በተለይም የምርመራው ሥራን ወይንም የክስ ሥራው የሚያከናውነው አካል በእነዚህ መንግሥት ኃላፊነትን በአግባቡ ባልተወጡ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ሥራዎች ይሠራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎችን ወይንም ፋይናንሱን በተመለከተ ሕገ ወጦች ላይ የተወሰደ እርምጃና በቁጥር የሚገለፅ ነገር አለ?**

**አቶ ብሴን፡-** እንደገለፅኩልህ በተቋማችን ደረጃ ኬዞችን ፕሮዲዩስ አድርጎና ተገቢውን ትንታኔ አድርጎ ወደ ምርመራ አካል የማስራጨት ነው በዋናነት የምንሠራው።ከዚህ አንፃር ፖሊስ በተለይም ደግሞ የምርመራ ሥራውን ሲያከናውን እኛ ካገኘነው ግኝት ባሻገር ሰፊ የምርመራ ሥራ በመሥራት ተጨማሪ መረጃዎችን የማደራጀት ሥራዎችን ያከናውናል።በዚህ ሂደት ውስጥ የሚገኙ ተጨማሪ ተዋንያን እንዲሁም ጥቅም ላይ የዋለን ገንዘብ ጭምር የሚገኝበት ሁኔታ አለ።ምክንያቱ ደግሞ ፖሊስ የተለየ የምርመራ ቴክኒኮችን ስለሚጠቀም ይህንን ተከትሎ ሕጋዊ ሥርዓትን አስይዞና የሕግ ሂደቱን የመምራት ኃላፊነት ያለበት አቃቢ ሕግ ደግሞ እንዲሁ ሁኔታው ወደ ፍርድ ቤት አቅርቦ ተገቢው የሕግ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ይሠራል።

ስለዚህ በተጨባጭ በዚህ ድርጊት ውስጥ የተሳተፉ አካላት በስፋት የምርመራ ሂደት ላይ እንዳሉ አውቃለሁ።በተጨማሪም በተገቢው ፍርድ ሀብታቸው እስከ መውረስ ድረስ የደረሱ አካትም አሉ።ከዚህ በተረፈ እያንዳንዱ ጉዳይ ዝርዝርን በተመለከተ በፖሊስ፣ አቃቢ ሕግና ፍርድ ቤት ደረጃ ከተሄደ እነዚህን አሃዛዊ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በጥቁር ገበያ ላይ ዶላር መመንዘር አንዱ የወንጀል ድርጊት ነው። በዚህ ላይ ተቋማችሁ ምን እየሠራ ነው ?**

**አቶ ብሴን፡-** እንደሚታወቀው የሕግ አስከባሪ አካላት ይህን የጥቁር ገበያን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ሰፋፊ ሥራዎችን እየሠሩ ነው።በቅርቡ ኅብረተሰቡ እንደሚገነዘበው በዚህ ድርጊት ላይ የተሳተፉ አካላት ላይ መወሰድ የጀመረ ጠንካራ እርምጃ አለ።ለአብነትም ማንሳት ከተፈለገ ለዚህ ጥቁር ገበያ የሚውሉ በሺዎች የሚቆጠሩ የባንክ ሂሳቦች የመዘጋትና በዚህ ድርጊት ላይ የተሳተፉ አካላትን በሕግ ለመጠየቅ ምርመራዎችና ሂደቶች ቀጥለዋል።ስለዚህ እንደሕግ አስከባሪ ተቋም ሥራዎች እየተሠሩ ነው፤ በቀጣይም መጠናከር አለባቸው።እንደሚታወቀው ባንኮች አካባቢ ሲኬድ እጥረት ስላለባቸው ዜጎች ለሚፈልጉት ዓላማ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ይቸገራሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ባንኮች የውጭ ምንዛሪ የማይሰጡት እጥረት ስላለባቸው ወይስ ደካማ አሠራርና ሙስና ስለተስፋፋ?**

**አቶ ብሴን፡-** በተቋም ደረጃ ያሉ ግለሰቦች ሕገ ወጥነትን በሚያበረታታ ድርጊት ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ።እነዚህ አካላት ላይ ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግ አስተማሪ እርምጃ እንዲወሰድ እንደ መንግሥት ውሳኔ ተላልፏል።በተለይም በባንኮችና በፋይናንስ ተቋማት ያሉ የባንክ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በመሰል ድርጊት ላይ እንደሚሳተፉ ኅብረተሰቡ የተለያዩ ጥቆማዎችንና ሃሳቦችን ይሰጣል።በዚህም ላይ ሲሳተፉ የነበሩ በርካታ ሰዎች በሕግ ቁጥጥር ስር ውለዋል።ስለዚህ ሕጋዊ የባንክ ሥርዓቶችን በመጠቀም የሚፈፀሙ ሕገ ወጥነቶችን የመቆጣጠርና የመከታተል ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ የባንኩ ሥራ ነው።

በአዋጅ 782/2005 ላይ እንደተቀመጠው በሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር የፋይናንስ ወንጀል የፋይናንስ ተቋማት መጠቀሚያ እንዳይሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ የመከላከል ኃላፊነት ለተቋማቱ ተሰጥቷል።በዚህ መንገድ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡት ላይ እርምጃ ይወሰዳል።በዚህ ሂደት የተጀመሩ ሥራዎች አሉ።በመስሪያ ቤታችንና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች አሉ።በቀጣይነት እነዚህ ተቋማት የሕዝብ ተቋማት እንደመሆናቸው መጠን የሕገ ወጥነት መጠቀሚያ እንዳይሆኑ በተቋማት ውስጥ ተጠያቂነትን ማስፈን ያስፈልጋል የሚል የመንግሥት

# ተጠየቅ



ውሳኔ አለ።በመሆኑም የእኛም ሆነ የሌሎች ሕግ አስከባሪ አካላት እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል።ሁኔታዎች ካልተሻሻሉ በቀጣይ የሚወሰድ እርምጃ ስለማይቀር በተለይም በተቋማት ውስጥ የተቋማትን ሕጋዊ ሥርዓት ተከትለው ሕገወጥነትን በሚያራምዱት ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

**አዲስ ዘመን፡- በዲፕሎማት ሽፋን ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ስለመኖሩ ይነገራል።የውጭ ዜጋ ሆነው ሐሰተኛ ገንዘብ በማተም ተጠርጥረው የተያዙም አሉ።ተቋማችሁ በዚህ ረገድ ምን እየሠራ ነው፤ ይህ ወንጀል ስለመከናወኑስ የጠራ መረጃ አላችሁ?**

**አቶ ብሴን፡-** በውጭ አገር ዲፕሎማቶች በተመለከተ በተወሰነ ደረጃ የምናገኛቸው መረጃዎች እንዳሉ አውቃለሁ።ነገር ግን በሕግ አስከባሪ ደረጃ በእነዚህ አካላት ላይ ቁጥጥር ተደርጎ የተወሰደ ጠንካራ እርምጃ የለም።

**አዲስ ዘመን፡- ለምን ጠንካራ እርምጃ አልተወሰደም?**

**አቶ ብሴን፡-** እነዚህን ተግባራት በማከናወን ሂደት በወሳኝነት ኃላፊነቱ በአካባቢው የሚገኙ የሕግ አካላት ናቸው።ስለዚህ አንድ ተቋም ሌላውን ወክሎ መረጃ መስጠት ተገቢ አይደለም።መሰል መረጃዎችን በአካባቢው ባሉ ፖሊሶችና የፖሊስ ተቋማት የሚያከናውኗቸው ክትትሎችና ምርመራዎች የሚፈፀሙ ተግባራት ናቸው።የእኛ ተቋም መረጃ ክትትል በማሰማራት የራሱን ሥራ ይሠራል።ነገር ግን ሕግ አስከባሪ ተቋማት የሚወስዷቸው እርምጃዎችና ክትትሎች አሉ።መረጃዎችንም ከእነዚህ አካላት በቀላሉ ማግኘት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በፋይናንስ ደህንነት ረገድ ኢትዮጵያ ያለችበት የጂኦ ፖለቲክስ፣ የምሥራቅ አፍሪካ ሽብርተኝነት ስጋትና የመሳሰሉትን ሁኔታዎች ያገናዘበ ሥራ እየተሠራ ነው ማለት እንችላለን?**

**አቶ ብሴን፡-** ትክክል ነህ።በተለይም ደግሞ በምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ላይ ከፍተኛ የሆኑና ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንጀሎች የሚካሄዱበት ነው።ከዚህ አንፃር የሽብርተኞች እንቅስቃሴ አለ።በዚህም ሁኔታ ለእነዚህ አካላት የሚሆን ገንዘብ እንዳይተላለፍ ጠንካራ የሆነ ፀረ ሽብር የፋይናንስ ሥራ ማከናወን ያስፈልጋል።ሕገ ወጥ የሰዎች እና ገንዘብ ዝውውር የሚካሄድበት ሁኔታ አለ።ሰፋፊና ዓለም አቀፍ ወንጀሎችን ለማካሄድ ብዙ ተዋንያን የሚንቀሳቀሱበት ቀጣና መሆኑ ይታወቃል።ከዚህ አንጻር ሥራዎችን ቀጣናዊ በሆነ ተቋም አማካኝነት በጋራ የመሥራት እንቅስቃሴ አለ።በተለይ ከምሥራቅ እና ደቡባዊ አፍሪካ ቀጣና አንፃር የተቋቋመ ተቋም አለ።ይህም ተቋም የምሥራቃዊና ደቡባዊ አፍሪካ ፀረ-ገንዘብ ዝውውር ይሰኛል።

በዚህ ተቋም ይህ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ጨምሮ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመደገፍ ወንጀሎችን አገራቱ በተለይም አባል የሆኑ 18 አገራት አሉት።አገራቱ በተናጠልና በጋራ እነዚህን ወንጀሎች ለመከላከል በጋራ ይሠራሉ።በመደበኛ የሚገናኙበት፣ ሥራዎችን የሚገመግሙበትና የጋራ ኃላፊነት መወጣት የሚችሉበት መድረክ አለ።በዚህ መልኩ እንደ አገር በተናጠል የምናከናውነው ነገር አለ።ቀጣናዊ በሆነ መልኩ ከጎረቤት አገራት ጋርም የምንሠራቸው ሥራዎች አሉ።መረጃዎችን ገደብ ሳይኖር በስፋት እንለዋወጣለን፤ ከአንዳንዶቹ፣ ጋር የሁለትዮሽ ሥምምነት ተፈራርመናል።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ኢትዮጵያን የማተራመስ ፍላጎትን ለማሳካት በስተጀርባ ገንዘብ ኢንቨስት ማድረግ ነው።ከዚህ አኳያ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ብሴን፡-** አዎ ልክ ነው።በዋናነት ይህ ሥራ ሊገለፅ የሚችለው ከአገራችን ታሪካዊ ጠላቶች አንፃር፤ በአገር ውስጥ ያሉና ሕገ ወጥ ተግባራትን ለሚያከናውኑት ድጋፍ በመስጠት ሊገለፅ ይችላል።በዚህም ሕግ አስከባሪ አካላት ጉዳዩን በትኩረት ይከታተሉታል።ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር የሚንቀሳቀሱ አካላትን በገንዘብ ለመደገፍ የሚሠሩትን በንቃት የመከታተል ሥራ አለ።

በዚህ ረገድ እንደ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ያሉ ተቋማት ይህን ድርጊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በስፋት ይንቀሳቀሳሉ።የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ደግሞ በተለይ ሕጋዊ የፋይናንስ ሥርዓትን ሽፋን ተከትሎ ሊመጡ የሚችሉ ተጋላጭነትን እንዳይኖር ለማድረግ ተከታታይ የቁጥጥር ሥራ ይሠራል።ድንበር አካባቢ ደግሞ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኢሚግሬሽና ዜግነት መምሪያ ከመሳሰሉት ተቋማት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ክትትሉና ቁጥጥሩ ይሠራል።በዚህ ረገድ እንደ አገር ቅንጅታዊ አሠራር አለ፤ በጋራም አፈፃፀም ይገመገማል።ኢትዮጵያ በርቀት ያሉ ታሪካዊ ጠላቶቿን ሁኔታ መመከት ብቻ ሳይሆን በዙሪያዋ ያሉ ጎረቤት አገራትና የኢትዮጵያ ሠላም ይገዳቸዋል ከምንላቸው ጭምር በጋራ እንሠራለን።ድንበር በመሻገር መረጃ ማግኘትና ጉዳትን ቀድሞ መከላከል እየተቻለ ነው።በተለይ ደግሞ በዚህ ወቅት ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ዘመን በአደጉት አገራት ጭምር የወንጀል አድራጊዎች አቅም ከተቋማት አቅም በላይ እየሆነ መምጣቱ ይነገራል።የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ከሚቃጡት ጥፋቶች አኳያ አቅሙ ምን ደረጃ ላይ ነው?**

**አቶ ብሴን፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው።ተቋሙ በመንግሥት ደረጃ ያለውን ሚና በመገንዘብ ድጋሜ ተጠናክሮ ማቋቋምና ማስቀጠል በመታመኑ ባለፈው ዓመት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ተቋቁሟል።ተቋሙ ተልዕኮውን የሚመጥን ቁመና እና የሰው ኃይል እንዲኖረው ለማድረግ ትልቅ ውሳኔ ተወስኗል።ይህም በቂ ባለመሆኑ ከችግሩ ውስብስብነት ጋር የሚመጥን ወንጀልን መከላከል አቅም በተለይ ደግሞ ከቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ሥራዎችን መሥራት ስለታመነበት እንደ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት (ኢንሳ) ካሉ ተቋማትና ሌሎች ቴክኖሎጂ ከሚያበለፅጉ ተቋማት ጋር ችግሩን በቴክኖሎጂ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እየተሠራ ነው።

የፋይናንስ ተቋማት ጋር በቀጥታ መረጃ ለማግኘት የተዘረጋ የቴክኖሎጂ ሥርዓት ብሎም በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓትና ከመንግሥት ተቋማትም መረጃ የሚገኝበት ሥርዓት ሰፊ ሥራ ተሠርቷል።በአሁኑ ወቅት በተሻለ ኃላፊነት ለመወጣት እየተሠራ ሲሆን የሰው ኃይል አቅም ለመገንባት የተቋሙ ሠራተኞችን ከአገር ውጭ ዓለም አቀፍ ስልጠና እየወሰዱ ነው።ተቋሙ የሰው ኃይል ብዛትና ብቃቱም እያደገ ነው።በቀጣይ እየተጠናከረ የሚሄድ ሲሆን፤ የመንግሥትም ድጋፍ በየጊዜው እየተጠናከረ ነው። አሁን ካለው በላይ ችግሩን የሚመጥን ተቋማዊ ግንባታ ያስፈልገናል፤ በዚህም በስፋት እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሌላው የዘመኑ ፈተና ምናባዊ ገንዘብ ነው የሚል ስጋት አለ።ያደጉ አገራት ምናባዊ ገንዘብ በሚል እየገበያዩና በርካታ አገራትን እያጥለቀለቀ ነው።በዚህ ላይ ኢትዮጵያ ምን እየሠራች ነው?**

**አቶ ብሴን፡-** በርካታ አገራት በተለይም ያደጉ አገራት ቀደም ብለው አይቀሬ የሆነውንና በእኛ አገር ቢትኮይን፤ ክርፕቶ ከረንሲ እና የተለያዩ ስያሜ የተሰጧቸው ሲሆን በሙያዊ አጠራር ደግሞ ቨርቹዋል ወይንም ምናባዊ ገንዘብ በሚል ይወሰዳል።ያደጉ አገራት በየራሳቸው ሕግና ቁጥጥር አበጅተው በሕጋዊ ፈቃድ እየሠሩ ነው።በየአገራቱም ከፋይናንስ ሥርዓታቸው ጋር አጣጥመው እየሠሩበት ሲሆን፤ በርካታ የአፍሪካ አገራት ይህን አሠራር ተግባራዊ እያደረጉ ነው።

ስለዚህ የዚህን ገንዘብ ባህሪ ያገናዘበ የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።ይህንንም በአግባቡ ተገንዝበን ወደ ሕገወጥነት እንዳይሄድ የሚቆጣጠር ተቋም ያስፈልጋል።በእኛም ሁኔታ እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ የፋይናንስ ሥርዓት ሕግ መሠረት የኢትዮጵያ ብቸኛው መገበያያ ገንዘብ የኢትዮጵያ ብር ብቻ ነው።ከዚህ ውጪ ያለ ማንኛውም ግብይት ሕገ ወጥ ነው።ከዚህ አንፃር ራሱን የቻለ የሕግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።በአሁኑ ወቅት በምናባዊ ገንዘብ ኢትዮጵያ ውስጥ ግብይት መፈፀም ወንጀል ነው።መሰል እንቅስቃሴዎችን ስናስተውል በብሔራዊ ባንክ በኩል ሕገ ወጥ ስለመሆኑ ለኅብረተሰቡ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን እንደ መንግሥትም መግለጫ እየተሰጠበት ነው።

ምናባዊ ገንዘብ ግብይት በኢትዮጵያ ቢፈቀድና ባይፈቀድ ምን ጥቅምና ጉዳት አለው የሚለውን ለማወቅ የተጋላጭነት ጥናት እየተካሄደ ነው።የዓለም ባንክም በዚህ ረገድ ቴክኒካዊ ድጋፍ እየሰጠ ነው።የሚመለከታቸው የሕግ አስከባሪ ተቋማትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ያሉበት የጥናት ቡድን በማቋቋም ጥናቶች እየተካሄዱ ነው።በሂደት ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ ላይ በምን ዓይነት ሁኔታ እየተካሄደ ነው ጉዳቱ ምንድን ነው፤ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ የጥናቱ ውጤት ያሳያል።ከዚህም በመነሳት ተቋማዊና የሕግ ማዕቀፎች ምን መምሰል አለባቸው የሚለውንም ጭምር የጥናቱ ውጤት የሚያሳይ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገቡ ፍንጭ ተሰጥቷል።ከዚህ አኳያ የፋይናንስ ሥርዓቱ እንዳይታወክና ከታለመው ዓላማና ቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ብሴን፡-** እነዚህ የፋይናንስ ተቋማት ከተለመደው ወጣ ያሉ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ።የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው ሲሆን ትስስራቸው ዓለም አቀፋዊና ቅርንጫፎቻቸው ከአገር ውጭ ሊኖሩ ይችላል።በዚህ ረገድ የእነዚህን አካላት እንቅስቃሴ መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ በመንግሥት ደረጃ የሕግ ማዕቀፍ የዝግጅት ሥራ እየተከናወነ ነው።ይህን የሚቆጣጠረውም በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የራሱን ሕጎች ያወጣል።

ከፋይናንስ ወንጀሎች አኳያ ደግሞ የእኛ ተቋም የራሱን ሕግ ማዘጋጀት ይኖርበታል።ለዚህ ደግሞ በቂ ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችል ሥራ ተጀምሯል።የልምድ ልውውጦችን ማካሄድ፣ ጥናቶችን ማከናወንና የመሳሰሉ ሥራዎችን ከወዲሁ ጀምረናል።የትኞቹ ባንኮች ይምጡ ምን ያህል በአገር ውስጥ ይስሩ የሚለው ነገር ከወዲሁ የሚታወቅ ባይሆንም በመንግሥት ደረጃ አስቀድሞ ተቋማዊ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በኩል የተሄደበት ነገር እንዳለ ሆኖ፤ በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎትም ዝግጅት የማድረግና ሁኔታዎችን የማጤን ጅምር መኖሩን መግለፅ እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ፤ ተጨማሪ ሐሳብ ካለ ዕድሉን ልስጥዎት።**

**አቶ ብሴን፡-** እነዚህ ወንጀሎች በተወሰኑ ተቋማትና ጥንካሬና ጥረት ብቻ መከላከል አይቻልም።ከዚህ አንፃር የኅብረተሰቡ ሚና ትልቅ ዋጋ ይሰጠዋል።የወንጀሉ መንስራፋት የሚጎዳው ሕዝብና አገርን ነው።ኅብረተሰቡ የሚሰጠው መረጃ አለ፤ ይህንን ማጠናከር አለበት።በተለይ በሕገ ወጥ ገንዘብ ዝውውር፣ የጥቁር ገበያ ምንዛሪ የተነሳ የኑሮ ውድነት ይስተዋላል።ይህ ኅብረተሰቡን በቀጥታ እየጎዳ ነው።በመሆኑም መሰል ድርጊት በመንግሥት ጥረት ብቻ ስለማይሸፈን ማህበረሰቡ ከጎናችን በመሆን ሥራችንን እና ጥረታችንን እንዲያግዝ ብሎም ለእነዚህ ሕገ ወጥ አካላት ምቹ ሁኔታ እንዳይፈጠር መሥራት አለበት፤ እንደ ተቋምም ጥሪያችን ማስተላለፍ እንወዳለን።

**የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት በተለይ ሕጋዊ የፋይናንስ ሥርዓትን ሽፋን ተከትሎ ሲመጡ የሚችሉ ተጋላጭነትን እንዳይኖር ለማድረግ ተከታታይ የቁጥጥር ሥራ ይሠራል**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "የፍል ውሃ ዋናተኞች"

**የማዋዣ ወግ፣**

የባህርይ ጥናት ተመራማሪዎችና የአነቃቂ ንግግር ባለተሰጥዖዎች ዕንቁራሪትን አስመልክተው የሚጠቅሱት አንድ የተዘወተረ ምሳሌ አለ:: ምሳሌው በትንሽ በትልቁ ዘንድ በሚገባ የሚታወቅ ቢሆንም ለዚህ ጽሑፍ ማጎልበቻነት የሚመጥን መስሎ ስለታየን ደግመን እናስታውሰዋለን:: በሰሞንኛው የውሎ አምሽቷችን ተግባቦት (Communication) ዋነኛ አጀንዳ አድርገን እንደ ኅዳር ጭስ "እየታጠንበት" ላለው "የልብ ትርታችንም" የምሳሌው ዐውዳዊነት ገላጭ ስለሆነ ከርዕሰ ጉዳያችን ጋር በሚገባ የሚጎዳኝ ይመስለናል::

"አንዲትን ዕንቁራሪት በሰፊ የብረት ድስት ገበቴ በተሞላ ውሃ ውስጥ ጨምረን እሳት ላይ ብንጥዳት ዘልዬ ካልወጣሁ ብላ ላትወራጭና ላትንፈራገጥ ትችል ይሆናል:: ምክንያቱም ውሃው ለብ እያለ ሲሄድ በሙቀቱ ምክንያት ስለምትዘናጋ በፍል ውሃው ነፍራ እስክትገነትር ድረስ አብጣ ብትነረትም የድሎትና የተዝናኖት ውጤት ስለሚመስላት እየሞተች መሆኗ እንኳን ትዝ ላይላት ይችላል::"

"ዕንቁራሪት ዝሆንን አከላለሁ ብላ ፈነዳድታ ሞተች" የሚለው ብሂል መነሻው ይህ ታሪክ ሳይሆን የሚቀር አይመስለንም:: ካልሆነም ምሳሌውንና ብሂሉን ብናዛምዳቸው ክፋት የለውም:: በአንጻሩም ያቺውኑ ዕንቁራሪት በፈላ ውሃ ውስጥ ብንከታት ሙቀቱና ፍላቱ እንግዳ ስለሚሆንባት ዘልዬ ካልወጣሁ ብላ አጥብቃ መንፈራገጧ አይቀርም::"

**የፍል ውሃ ዋናተኞቹ የሀገሬ ሙሰኞችና ሌቦች፤**

የመንደርደሪያችንን ማዋዣ እዚሁ ላይ ገታ አድርገን ወደ ዋነኛው ጉዳያችን እንዝለቅ:: ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሰሞኑ የፓርላማ ንግግራቸው ያስጨበጨበላቸውን አንድ ጉዳይ በግልጽነት ነግረው አደፋፍረውናል:: ንግግራቸው ጭል ጭል የምትለው የተስፋችን ኩራዝ ደመቅ ብላ እንድትበራም ምክንያት የሆነ ይመስለናል:: በቁርጠኝነት ይፋ ለገለጡትና በክፉ ነቀርሳነት ለሚመሰለው ሀገራዊ የሌብነት ፈተናችን ማስታገሻነት ለተሰጠው መንግሥታዊ ውሳኔ ባናመሰግን ባለ ዕዳ እንሆናለን:: በተለየ ሁኔታ ግን "የማይታለፈው ቀይ መስመር ወደ ቀይ ምንጣፍነት መለወጡን" የገለጹበት አነጋገር በዚህ ጸሐፊ ግምት የዓመቱ ድንቅ ገለጻ ሆኖ ቢመዘገብ ይበዛበታል የሚባል ዓይነት አይደለም::

እንደኛዎቹ ጉደኛ ሌቦች የሕዝብና የሀገር ሀብት በመዝረፍ የተካኑ የሌሎች ሀገራት መሰል የሌብነት ባለ ታሪኮች ይኑሩ ወይንም አይኑሩ ለማወቅና ለማነጻጸር ምርምርና ፍተሻ ማድረጉ እጅግም የሚጠቅም አይደለም:: መኖሩ ቢያጠራጥረንም "ሞልቶ" ብለው ለሚሟገቱ ተከራካሪዎች የውይይቱን በር ላለመዝጋት ሲባል ብቻ የሚያውቁትን ቢያሳውቁን ለዕውቀትም ሆነ ለጸሎት ሊረዳ ስለሚችል በየት ሀገርና እንዴት እንደሆነ ቢነግሩን አይከፋም:: ይህንን የምንልበት አጥጋቢ ምክንያት ስላለን መከራከሪያችንን እናብራራለን:: ብሶታችንን በነፃነት ዘርግፉ ስለተባልን "ሀገር ያወቃቸውን፤ ፀሐይ የሞቃቸውን" አንዳንድ "የአደባባይ ምሥጢሮችን" ብቻ ለማሳያነት ለመጠቋቆም እንሞክራለን እንጂ ችግሩን ሁሉ አሟጠን እንዘረዝራለን ማለት አይደለም::

በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ አካባቢዎችና ጥቂት በማይባሉ የክልል ከተሞች ውስጥ "የሙስና ሠፈር" የሚባሉ አካባቢዎች መኖራቸውን መንግሥት "አልሰማሁም፤ አላወቅሁም" ብሎ የኢትዮጵያን ስም እየጠራም ሆነ ሕገ መንግሥቱ ላይ እጁን ጭኖ ቢምል ቢገዝት እንኳን ልንሰማው ቀርቶ ጉዳዬ ብለን ጆሯችንን ለመስጠትም ይቸግረናል:: ምክንያቱም በሚገባ ያውቀዋል:: መረጃውም በእጆቹ ላይ ናቸው::

**በአዲስ አበባ ከተማ በአንዳንድ አካባቢዎችና ጥቂት በማይባሉ የክልል ከተሞች ውስጥ "የሙስና ሠፈር" የሚባሉ አካባቢዎች መኖራቸውን መንግሥት "አልሰማሁም፤ አላወቅሁም" ብሎ የኢትዮጵያን ስም እየጠራም ሆነ ሕገ መንግሥቱ ላይ እጁን ጭኖ ቢምል ቢገዝት እንኳን ልንሰማው ቀርቶ ጉዳዬ ብለን ጆሯችንን ለመስጠትም ይቸግረናል:: ምክንያቱም በሚገባ ያውቀዋል:: መረጃውም በእጆቹ ላይ ናቸው::**

አልፎም ተርፎ የአካባቢዎቹ ስያሜ በሕግ የተፈቀደ እስኪመስል ድረስ "የሙስና መንደር" እየተባለ በሕጋዊ ሰነዶች ሁሉ ላይ ሳይቀር የሚጠቀሱላቸው አካባቢዎች ብዙዎች ናቸው:: ጠቢቡ ባለሀገር "የጉድ ሀገር ገንፎ እያደር ይፋጃል" ማለቱን ወድጄለታለሁ:: እናስ ለሌብነት እንዲህ ዓይነት ዕውቅና የሰጠ ሌላ ሀገር አለ ቢባል ማን ይቀበላል?

ሁለተኛ፤ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች ላይ እየተንፈላሰሱ ጌቶቻቸውን የሚያንፈላስሱት ሽንጠ ረዣዥሞቹ አብዛኞቹ በምንትስ ብራንድ የሚታወቁት የፒክ አፕ መኪኖች (የጥቂት ላብ አደር ‹?› መኪኖችን ፍረጃው አይመለከትም) ስያሜያቸው የሙሰኞችና የደላሎች መባሉን መንግሥታችን አልሰማ ይሆን? ባለንብረቶቹስ እየመነዘሩ መኪኖቹን ንብረታቸው ያደረጉት የሕዝብ እምባ እየሰፈሩ መሆኑ አይታወቅምን? "ከኑግ ጋር የተገኘሽ ሰሊጥ አብረሽ ተወቀጭ" በማለት ጥቂት ጨዋ ንጹሐን አብሮ ስማቸው እንዳይነሳ አደራ እንላለን::

"እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን" የሚለው ደርጋዊ ብሂል ዛሬም በሠላሳ ዓመቱ መልዕክቱ እንዳልደበዘዘ ስለምንጠረጥር የምንተነፍሰው የብዕራችንን ልጓም ገታ በማድረግ ነው:: መንግሥት መረጃው የለኝም የሚል ከሆነ (እንደማይል ተስፋ በማድረግ) የትራንስፖርት ቢሮዎችን ዶሴ በመመርመር "ንጹሐንን እንዲያመሠግን፣ ዘራፊዎችን እንዲለይ፣ ግፉዓንን በፍትሕ እንዲዳኝ" አቤቱታ እናቀርባለን::

ለመሆኑ ስሙ ቤትኛ፣ ተግባሩ እንደ ሰማይ የራቀብን የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ጉዳይስ ዝም ተብሎና ተድበስብሶ ሊያልፍ ይሆንን? ሀገር እንዲታደግ ከላይ እስከ ታችኛው የሀገሪቱ ዳርና ጠረፍ ድረስ በመንግሥት መ/ቤቶችና በልማት ተቋማት ውስጥ መዋቅሩ ተዘርግቶ የሀገሪቱ ሀብት ሲፈስለት የኖረው ኮሚሽን ዕድል ፈንታው ምን ሊሆን ነው? ጠይቁ ስለተባልን እንጠይቃለን፣ አትጠይቁ ከተባልንም ዝምታችንን እያመነዠግን ቀን እንገፋለን::

በየሚዲያው ማስታወቂያ እያስነገረ ሲያደነቁረን የታገስነው "የፌዴራሉ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን" ወይ እንደ ስሙ ይጀግን አለያም ስሙን ለሰጠው አካልና ሀገር መልሶ በማስረከብ እንደ ፍጥርጥሩ ይሁን:: ለምሳሌ፡- "የመንግሥት ሹመኞችንና የሕዝብ ተመራጮችን ሀብት እመዘግባለሁ እያለ እንዳልፎከረ ስለምን እንደ ቃሉ ሪፖርቱን በግላጭ ለሕዝብ ይፋ አላደረገም? የሰነፍ ዱላ ዘጠኝ ነው እንዲሉ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የመንግሥት ሠራተኞችንም ሀብት ጨምሬ እመዘግባለሁ ብሎ ምኞቱን ከፍ ማድረጉ አይዘነጋም:: እኮ ስለምን በመሐላ ጭምር የገባልንን የተስፋ ቃሉን ቅርጥፍ አድርጎ ሊበላ ቻለ? መልስ ባናገኝም መጠየቃችንን ሳናቆም "ልብ አድርጉልን" በማለት ለታሪክ እማኝነት እያስመዘገብን እናልፋለን::

ከሰሞኑ የተቋቋመው "የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ" ጉዳይ ከዚህ በተግባር ሳይሆን በዕድሜ ርዝመት ካፈጀው ተቋም ጋር ያለው የስምና የተግባር መወራረስና መለያየት እስከ ምን ደረጃ እንደሆነ እስካሁን አልተገለጸልንም:: ግማሽ ሥልጣኑ ተገምሶ የተወሰደበት ተቋሙ የቀረው ከፊል ጎኑ "ሥነ ምግባር" የሚለው ብቻ እንደሆነ ባያስረዱንም ገብቶናል:: ለማንኛውም አዲሱ ጎጆ ወጭ ብሔራዊ ኮሚቴ የት ድረስ እንደሚዘልቅ ለጊዜ ጊዜ ሰጥተን በትዕግሥት እንጠብቃለን:: ሕዝቡ መረጃ እንዲያቀብል ተለይቶ የተሰጠው ባለ አራት ዲጂት 9555 የስልክ መስመርም እንደ ጓደኛው እንደ ኤሌክትሪክ አገልግሎቱ 905 ልሳኑ ተዘግቶ ዲዳ ሆኖ እንዳያበሳጨን ከወዲሁ ሕዝባዊ መልዕክታችን ይድረስልን እንላለን::

ወደ ዕንቁራሪቷ ጉዳይ እንመለስና ከዚህ ክፉ የማኅበረሰብ ነቀርሳ ከሆነው የሌብነትና የሙስና ጉዳይ ጋር እያስተያየን ጥቂት እንቆዝም:: ዛሬ በሀገሪቱና በሕዝቡ ላይ እንደ መዥገር ተጣብቀው መቅኒውን የሚመጡት (ደሙ፣ ሥጋና አጥንቱማ ተግጦ ያለቀ ይመስላል) ክፉ የቀትር ጋኔን ሌቦች ዘረፋቸውን የጀመሩት ትናንት አይደለም:: ሥራቸው እጅግ የረዘመና ሴራቸውም እጅግ የተወሳሰበ ነው:: እንደ ዕንቁራሪቷ ፈነዳድተው እስኪሞቱ ድረስ ዘረፋውን የተለማመዱት ቀስ በቀስ ነው:: ለዛሬው አበሳችን በይደር የተላለፈው አሳርም "ያኔ በዕንቁላሉ ጊዜ" ስላልተቀጡ፤ እንዲቀጡም ባለመፈለጉ እንጂ ከልብ ቢታሰብበት ኖሮ የሀገሪቱ መከረኛ ፊት እንደዛሬው ባልገረጣ ነበር:: የሀገራችንን ሌብነትና ሙስና የምንመስለው በፍል ውሃ ዋና ነው:: ይዋል ይደር እንጂ የፍል ውሃው ዋናተኛ ሌቦች ሕሊናቸውና መንፈሳቸው፣ ነፍስና ሥጋቸው ገንትሮ ወደ ሲዖል እንደሚወርዱ የምንመሰክረው የምድሩንም የሰማዩንም ፍርድ እያጣቀስን ነው::

ብዕረኛው ወዳጄ ክፍሌ አቦቸር (ሻለቃ) እያነባ ከከተበልን ግጥሞች መካከል (እንባውን ሲያፈስ ያይን ምስክር ስለነበርኩ) ከዚህ መልዕክት ጋር በሚገባ የሚጎዳኙትን ዘለግ ያሉ ስንኞች እየመረጥሁ ላስታውስ፤

**"አረማመዱ የሚነቀል ማስዳ ነው ከቡቃያው፣**
**ከጥንቱ ነው ከችግኙ አበባውም የሚጠጣው፣**
**ጠማሞቱ የሚቃናው፡፡**
**እንጂማ፡- ኮትኳች ከሴስ አረም ነቃይ፣**
**ወሳጅ ከሴስ ተቀባይ፣ ጥሩም መጥፎውም**
**አይታይ፡፡**
**ይኼው ነው የእኛም ነገር፣—ሀ" ሲባል —ሀ" ቢባል፣**
**ጅምሩ ቀድሞ ቢዳሰስ፣ ቀድሞ ቀድሞ ቢቀነጠስ፣**
**መፈልፈያው ቢደፈን፣ ሥሩ ማስዳ ቢበጠስ፣**
**ውስጥ ውስጡ የሳይ ሳዩ፣ቃርሚያው በወጉ ቢነሳ፣**
**ባልኖረ ባልነበረ የዛሬው ክምር አበሳ፡፡**
**ይኼው ዛሬም እንዲሁ፣ ለቆየን ችግር እርሾ**
**ሆኖን፣**
**እንደ ጲላጦስ አንጡኝ የሚል የውስጡን**
**በውስጡ ይዞ፡፡**
**የችግሩ "ችግር" ይህ ነው፣ ሽምቅታው ነው**
**የበደለን፣**
**የሳመን ነው የነከሰን፣ የሳቀ ነው የገደለን፡፡**
**እና ጎበዝ! ያለፈው ቀድሞ አለፈ**
**ዛሬ ለነገ እንዲቀነስ፣ ድራ ድሩን ነው መበጣጠስ፣**
**"አስኳሉን" ነው መፈርከስ፡፡**
**እንጂማ፡- ቅርንጫፉማ ጭራሮ ነው፣**
**ግንዱ ሲቆረጥ የሚረግፍ፣ግንዱም ቢሆን**
**ግንዲሳ ነው፣**
**ሥሩ ሲነቀል የሚነጥፍ፡፡**
**የሚሆነው ዛሬ ይሁን፣ አይኑር "ይደር"**
**የምንለው፣**
**"ከመፈቅፈቅ ማለቅለቅ" እንዲሉ ነውና አበው፡፡**

የሀገራችን የሙስናና የሌብነት ታሪክ መልኩና ምስሉ በዚህ ግጥም ውስጥ ከተንፀባረቀው እውነታ የሚለይ አይደለም:: ሌቦቹ ለብ ባለ ዘረፋ ውስጥ ሲዘፈቁ ሙቀቱ የተስማማቸውና ለብታው የተመቻቸው ገና በማለዳው እንዳልታዩ ስለታለፉ ነው:: እውነቱ ግን ሌባ የሰረቀው የሚጣፍጠው ከጉሮሮው እስኪወርድ እንጂ ወደ ከርሱ ከዘለቀ በኋላ ለሕሊናው ካንሰር ሆኖ እንደሚያሰቃየውና እንቅልፍ ነስቶ እንደሚያባንነው በግልጽ ይታወቃል:: ለምን ቢሉ ሌብነት የፍል ውሃ ዋና ስለሆነ ውሎ አድሮ ማፈነዳዳቱ አይቀርም::

ሌብነት ተዋራጅነት ነው:: እንደዚህ ጸሐፊ እምነት ቢሆንማ መንግሥት በቀጥታ ያገባኛል በሚላቸው ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን በየሃይማኖት ተቋማትም ውስጥ ሳይቀር በዐውዳቸው ልክ "የቤተ እምነቶች ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ" አቋቁሞ ፍተሻው ቢቀጥል ምንኛ መልካም በሆነ ነበር:: ለመቶ ፐርሰንት ጥቂት ፈሪ ቁጥር ባለበት ሀገር "መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው" የሚለው ገደብ ሁሌም ይህንን ጸሐፊ ከሕሊናው ጋር እንዳሟገተው ዘልቋል::

ሙስናን በተመለከተ "ውሻን ምን አገባው ከእርሻ" የሚሉትን ብሂል እያስታወሱ ከቶውንም ቢሆን መንግሥትን ይህ ጉዳይ አያገባውም ማለት የሚቻል አይመስለንም:: ስመ እግዚሐርና ስመ አላህ እየተጠራ ከምዕመኑ የሚሰበሰበው ሀብት ለታቀደለት ጉዳይ እንዳይውል የሚያደርጉ ሁሉ በሀገራዊው ሕገ መንግሥት ብቻም ሳይሆን በሚመሩባቸው ቅዱሳት መጻሕፍትም ጭምር ሳይቀር የሕግ ድጋፍ ስለሚኖር ጉዳዩ መንግሥትን ሊያስፈራውም ሆነ ሊያሳፍረው አይገባም::

በተለየ አትኩሮት ግን ከቀበሌ እስከ ዞንና ክልል ድረስ ባሉ እርከኖችና በአገልግሎት ሰጭ መንግሥታዊ ተቋማት ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ፣ ሕዝብም አራት ዐይናማ በመሆን የየድርሻን ኃላፊነት መወጣት ቢቻል ሀገራዊ መከራችን ሸክሙ ሊቀል ይችል ይመስለናል:: በኢትዮጵያ ምድር እዚህ ወይንም እዚያኛው ተቋም ውስጥ ሳልጉላላ ለያውም ተከብሬ ጉዳዬን ከውኜ ወጣሁ የሚል ዜና መደመጥ ሲጀምር ይህ ጸሐፊ ስዕለቱን ለፈጣሪ ምስጋናውን ለመንግሥት የሚያቀርበው በዕልልታ አጅቦ እንደሚሆን እነሆ ቃሉን በብዕሩ ያጸናል:: ሰላም ይሁን!

# የማዕድን ኤክስፖው ለገበያ ትስስር የነበረው ሚና

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የማዕድን ሚኒስቴር “ዓለም አቀፍ የማዕድን ኤክስፖ” ከሰሞኑ እንዳዘጋጀ ይታወቃል። በኤክስፖውም የማዕድን ኩባንያዎች፣ የጌጣጌጥ አምራቾችና ላኪዎች፣ የማዕድን ቴክኖሎጂ አምራቾችና አስመጪዎች እንዲሁም የፋይናንስ ተቋማት ተሳትፈውበታል። አምራቾችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ገዢዎች ጋር በቀጥታ ያገናኛል በሚል የተዘጋጀው ይህ ኤክስፖ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መዘጋጀቱ ተመላክቷል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው የማዕድን ኤክስፖ ከውጪ የሚመጡ የማዕድን ኩባንያዎች መሳተፋቸው በኢትዮጵያ ያለውን የማዕድን ኢንቨስትመንት አማራጭ እንዲመለከቱና የማዕድን ኢንቨስትመንት ላይ እንዲሳተፉ እድል የሚፈጥር ነው። ከዚህ በተጨማሪም የማዕድን ቴክኖሎጂ አምራቾች በኤክስፖው መሳተፋቸው ለኢትዮጵያ የማዕድን ዘርፍ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን የማስተዋወቅ እድል የሚፈጥር እንደሆነ ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

አምራቾችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ገዢዎች ጋር በቀጥታ በማገናኘት የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችላል በተባለው ዓለም አቀፍ የማዕድን ኤክስፖ በርካታ አምራቾች፣ ላኪዎችና የተለያዩ ኩባንያዎች ተገኝተዋል። ከእነዚህም መካከል በኤግዚቢሽኑ የኦፓል ምርት ይዘው የቀረቡት በርካቶች ነበሩ። በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ኤግዚቢሽኑ በመዘጋጀቱ ምርቶቻቸውን ይዘው ለመውጣትና ለማስተዋወቅ ሰፊ ዕድል የፈጠረላቸው መሆኑን በማንሳት በሀገሪቷ ያለውን የማዕድን ሃብት አይነትና መጠን ማኅበረሰቡ መረዳት እንዲችል ያደረገ ኤክስፖ መሆኑንም ሲገልጹ ተደምጠዋል።

ከተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች የከበሩ ማዕድናትን ይዘው በኤግዚቢሽኑ ከቀረቡት አምራቾች መካከል ከወሎ ደላንታ የተለያዩ የኦፓል አይነቶችን ይዘው የቀረቡት የጀምስቶን የማዕድን አቅራቢ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የማዕድን ልማት ባለሙያ አቶ ዑመር ሽፈሬ አንዱ ናቸው። አቶ ዑመር፤ የተለያየ መጠንና ይዘት ያላቸውን ኦፓሎች በኤግዚቢሽኑ ይዘው ቀርበዋል።

‹‹ጀምስቶን የማዕድን አቅራቢ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የደላንታ የኦፓል ምርቱን በኤግዚቢሽኑ ማቅረቡ ሰፊ የገበያ ዕድል የሚፈጥረለት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዑመር፤ በሀገሪቱ ያለው የማዕድን ሃብት እጅግ በርካታ እንደመሆኑ ብዙ ሊሠራበት የሚገባው ዘርፍ ነው። ዘርፉን ለማሳደግና ተጠቃሚ መሆን እንዲቻል የገበያ ትስስር መፍጠር ቀዳሚው ጉዳይ ነው በማለት እስካሁን ባለው ሂደትም በአካባቢው በቂ የሆነ የገበያ ትስስር አለመኖሩ ገልጸዋል።

በወሎ ደላንታ አካባቢ የተሻለ የኦፓል ምርት ስለመኖሩ የጠቀሱት አቶ ዑመር፤ በኤግዚቢሽኑ ለዕይታ ካቀረቧቸው የኦፓል አይነቶች መካከልም ክርስታል፣ ፖሊሽ ኦፓልና እርጥብ ገና ያልደረቀ ኦፓል የሚገኝበት መሆኑን አስረድተዋል። ምርቶቹ ለገበያ ለማቅረብ ከፍተኛ የሆነ የገበያ ችግር በመኖሩ መሰል ኤግዚቢሽኖችን ማዘጋጀት ለዘርፉ ዕድገት ጠቃሚ ነው። በተለይም የገበያ ትስስር ለመፍጠርና ገበያ ለማፈላለግ ሰፊ ዕድል የሚፈጥር እንደሆነ በማመን ምርቶቻቸውን ይዘው እንደመጡ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በነበራቸው ልምድ በአካባቢው የሚገኘውን የማዕድን ሃብት በተለይም ኦፓሎችን ለላኪዎች ይሸጡ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ኡመር፤ ኦፓሎቹ ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩት በላኪዎቹ አማካኝነት ነበር። ነገር ግን በአሁን ወቅት ድርጅቱ የማዕድን ሃብቱን በራስ አቅም ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ፈቃድ በማውጣት በዝግጅት ላይ ሲሆን ዓለም አቀፍ የማዕድን ኤግዚቢሽን መከፈቱ ጥሩ አጋጣሚ በመሆኑ የገበያ ትስስር የሚፈጥርና በማዕድን ዘርፉ አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮችን የማስተዋወቅ እድል ያሰፋል ብለዋል፡፡

መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት የማዕድን ሃብቱ አሁን ላይ የተሻለ እንቅስቃሴ እየታየበት እንደሆነ በማንሳት በተለይም ኤግዚቢሽኑ የሚፈጥረው ሰፊ የገበያ ዕድል ስለመኖሩ ነው ያስረዱት። በዕለቱም ለዕይታ ያቀረቡት ኦፓል እሴት የተጨመረባቸው ሲሆኑ ለገበያ የሚቀርቡትም በግራም እንደሆነ ነው ያስረዱት። ከፍተኛ መጠን ያላቸውና ለኢንዱስትሪ ግብዓት መሆን የሚችሉት ደግሞ በቶን የሚሸጡ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

የማዕድን ሃብቱ ከመሬት ውስጥ ተቆፍሮ የሚወጣና በሂደት ጸድቶና ደርቆ ለገበያ ይቀርባል። በአገሪቱ ደላንታ አካባቢ የሚገኘው ኦፓል አንደኛ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ተመራጭ እንደሆነ ነው የተጠቀሰው። በቀጣይ መንግሥት የገበያ ትስስሩን በማጠናከር ከተለያዩ ካምፓኒዎች ጋር መገናኘት የሚያስችሉ መሰል ኤግዚቢሽኖች ቢዘጋጁ ሰፋፊ የገበያ ዕድሎችን መፍጠር ይቻላል። የገበያ አማራጩም ከማዕድን ዘርፉ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍ ያደርገዋል ብለዋል።

የማዕድን ሃብቱ ከአምጪዎቹ በተከታታይ መቅረብ አለበት መቆራረጥ የለበትም የሚሉት አቶ ጌታቸው ታደሰ የጀምስቶን ማዕድን አቅራቢ ማናጀር በበኩላቸው የከበሩ ማዕድናት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በስፋት ይገኛሉ። እነዚህን ማዕድናት በማልማትና እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሀገሪቷ ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘት አለባት ይላሉ። የገበያ ትስስር መፍጠር ያስችላል በተባለው ኤግዚቢሽንም በወሎ አካባቢና ከሰሜን ሸዋ አካባቢ ያሰባሰቧቸውን የከበሩ የማዕድን አይነቶች ይዘው ቀርበዋል፡፡

እንደ አቶ ጌታቸው ገለጻ ኦፓሎቹ የሚገኙት በዋናነት ከወሎ ደላንታ ሲሆን ከሰሜን ሸዋ የሚገኘው የማዕድን ዓይነት ገበያ ውስጥ በስፋት አለመግባቱ ነው። ለዚህም ምክንያት ሲቆረጥ በቀላሉ የሚቆረጥና ጥንካሬው እምብዛም መሆኑ ነው። በመሆኑም በዋናነትና በስፋት ለገበያ እየቀረበ ያለው የወሎ ደላንታ ኦፓል ነው። ድርጅቱም ኦፓሉን እሴት በመጨመር አለስልሶ ለተለያዩ ጌጣጌጦች ጥቅም ላይ መዋል እንዲችሉ በማድረግ ለውጭ ገበያ እያቀረበ ይገኛል፡፡

በዋናነት ለጌጣጌጥ አገልግሎት የሚውሉት እነዚህ የከበሩ ማዕድናት በስፋት የሚፈለጉት፣በአውሮፓ፣ በጀርመን፣ በአሜሪካና በተለይም በሕንድ እንደሆነ አቶ ጌታቸው አስረድተው ድርጅታቸውም በአሁን ወቅት ማዕድናቱን በቀጥታ እየላከ መሆኑን ነው ያነሱት። ከዚህ ቀደም የከበሩ ማዕድናት ለላኪዎች ያስረክቡ እንደነበር በማስታወስ አሁን ላይ ሥራው እየተለመደ በመምጣቱ በርካታ ባለሙያዎችን በማሳተፍ እሴት ጨምረው በቀጥታ መላክ መጀመራቸውን ነው ያስረዱት፡፡

በተፈጥሮ ከከርሰ ምድር የሚገኙ የከበሩ ማዕድናት በብዛት በአገሪቱ ጥቅም ላይ ሲውሉ አይስተዋልም ለዚህም የማኅበረሰቡ የግንዛቤ እጥረት ነው የሚሉት አቶ ጌታቸው፤ በዋናነት ማዕድናቱ በሀገሪቱ ስለመኖራቸው ለኅብረተሰቡ ማሳወቅና ከሃብቱ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ በመሰማራት ከውጭ ባለሃብቶች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር ከራስ አልፎ ሀገሪቷ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ ያስችላል። ለዚህም በዘርፉ አስፈላጊና ተከታታይ የሆነ ስልጠና በመስጠት ባለሙያ በማፍራት ተገቢ እንደሆነ አስገንዝበዋል።

በኤግዚቢሽኑ መከፈቻ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ለተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ግብዓትነት የሚውሉ የከበሩ ማዕድናት ያላት ሀገር ናት። ይህንን ሃብትም ለሕዝብ ለማስተዋወቅና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚረዳ በመሆኑ የተለያዩ ኤግዚቢሽኖችን ማዘጋጀት ተገቢ እንደሆነ ነው የተጠቀሰው። በዕለቱም የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴ በተፈጥሮ ሃብቷ በተለይም ከመሬት ውስጥ ተቆፍሮ በሚወጣው የከበሩ ማዕድናቶቿ እጅግ ሃብታም ሀገር እንደሆነች ነው የተናገሩት፡፡

የእነዚህ የከበሩ ማዕድናት ሃብት ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደመሆኑ ሃብቱን በግላጭ መመልከት እንዲችል ኤክስፖው መዘጋጀቱን አድንቀው፤ ማኅበረሰቡ ማዕድናቱን እንዲያውቅ፣ ጠቀሜታቸውን እንዲረዳና አልምቶ መጠቀም እንዲችልም ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል በማለት ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ሀገሪቷ ያላትን ሃብት ከማስተዋወቅ ባሻገር ኤግዚቢሽኑ ሰፊ የገበያ ትስስር መፍጠርና የልማት ቴክኖሎጂ ልውውጥ ማድረግ የሚስችል በመሆኑ ሊበረታታ ይገባልም ብለዋል፡፡

‹‹ማዕድን በባህሪው አላቂ ሃብት እንደመሆኑ ያለንን ውስንና አላቂ ሃብት በአግባቡ መጠቀም ተገቢ እንደሆነና ዘርፉን ከሕገወጥ መንገድ መከላከል አስፈላጊ ነው›› ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ የማዕድን ዘርፉ በብዛት ለሕገወጥ ተግባር የተጋለጠ መሆኑን ገልጸዋል። በተለይም የማዕድን ሃብቱን በተለያየ መጠን ማልማት የሚቻል በመሆኑ በቀላሉ በሕገወጥ መንገድ ሃብቱን መጠቀም ያስችላል። ለዚህም ሕጋዊና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የአካባቢ ጥበቃን ማስጠበቅ በሚያስችል መንገድ መሥራት ከተቻለ በድህነት ውስጥ ያለውን ሕዝብ ከድህነት ማውጣት የሚስችል ዘርፍ እንደሆነ ነው ያስረዱት።





> **‹‹ማዕድን በባህሪው አላቂ ሃብት እንደመሆኑ ያለንን ውስንና አላቂ ሃብት በአግባቡ መጠቀም ተገቢ እንደሆነና ዘርፉን ከሕገወጥ መንገድ መከላከል አስፈላጊ ነው››**

የማዕድን ሚኒስቴሩ ኢንጅነር ታከለ ኡማ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሃብት ለበርካታ ዓመታት ሳትጠቀምበት መቆየቷን አንስተው በአሁን ወቅት ዘርፉ ላይ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ የሀገሪቱ ክፍለ ኢኮኖሚ የማድረግና ተጠቃሚነቷን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። እንደሳቸው ገለጻ፤ ማዕድን የሀገሪቱ ክፍለ ኢኮኖሚ ግንባታ እንደመሆኑ ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ በኮንስትራክሽን፣ በኢንዱስትሪና በሌሎች ዘርፎች ላይ የመጣው ለውጥ በማዕድንም እየመጣ መሆኑን አብራርተዋል። በሚቀጥሉት አስር ዓመታትም የማዕድን ክፍለ ኢኮኖሚ አሁን ለኢኮኖሚው እያዋጣ ካለው አንድ በመቶ ያልበለጠ ጂዲፒ ለሚቀጥሉት አስራ አራትና አስራ አምስት ዓመታት ከ17 በመቶ በላይ ሊያዋጣ የሚችል እንደሆነና ተስፋ የተጣለበት እንደሆነም ተናግረዋል።

ዘርፉን ለማሳደግ የሚረዱ አዋጆችና ፖሊሲዎች ተቀርጸው ተግባራዊ መደረጋቸውን የገለጹት ሚኒስቴሩ፤ በተለይም ከተለያዩ የውጭ አገራት የሚገቡ ውድና የከበሩ ማዕድናትን በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተሠራ ነው ብለዋል። ለዚህም ግልጽ፣ ሊያሠራና ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል የማዕድንና የፔትሮሊየም ፖሊሲ ተቀርጾ ሥራ መጀመር ተችሏል። ዘርፉን የሚመራው የማዕድን ሚኒስቴርም አስፈላጊ የሆኑ አዋጆችና መመሪያዎችን አደራጅቶ ከፌዴራል እስከ ክልል ማውረድ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ኤክስፖው መዘጋጀቱ የተለያየ የገበያ ትስስሮችን በስፋት ለመፍጠርና ምርቶቻቸውን ለማስተዋወቅ ሊያግዛቸው የሚያስችል ትልቅ ዕድል እንደሆነ የገለጹት የኤክስፖው ተሳታፊዎች እንዲህ አይነት ኤክስፖ በተለያየ ጊዜ ቢዘጋጅ መልካም እንደሆነ ጠቁመዋል። በዘርፉ የተሠማሩና ማዕድን አግኝተው የት መሄድ እንዳለባቸው የማያውቁ በርካታ ሰዎች ስለመኖራቸው በማንሳትም እንዲህ ያሉ መድረኮች ዘርፉን ይበልጥ ሊያስተዋውቁ ይችላሉ፡፡

እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች በተለይም የገበያ ትስስርን በመፍጠር ረገድ አበርክቷቸው ጉልህ መሆኑን በመግለጽም ገበያውና ምርቱም በቀጥታ የተገናኙበት እንደሆነ አንስተዋል። ኤክስፖው ማዕድናቱን ለማኅበረሰቡ ከማስተዋወቅ ባለፈ በአፍሪካ ደረጃ መዘጋጀቱ ሰፊ የገበያ ትስስር መፍጠር አስችሏል። በተጨማሪም ሲፈላለጉ የነበሩ የተለያዩ አካላትን በማገናኘት ጉልህ ሚና ያለው መሆኑንም አስረድተዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ጆሮ ትርፍ የሰውነት አካል ነውን?

ዋስልኝ አየለ

አሜሪካ ወይም የአውሮፓ ሀገራት ውስጥ የመኖር ዕድል ቢሰጠኝ መኖር የምፈልግበት ምክንያት አንድ ብቻ ነው። የረቀቀ ቴክኖሎጂ፣ ፈጣንና ምቹ መሠረተ ልማት ወይም ሌላ የሥልጣኔ መለያ የሆኑ ነገሮች ከሀገሬ ውጭ ለመኖር አጓጉተውኝ አያውቁም። የሰለጠኑ በሚባሉ ሀገራት የምቀናው በጤና የመኖር መብታቸውን ብቻ ነው።

ከአውሮፓ ሀገራትም ሆነ አሜሪካ የመጡ ሰዎች ካገኘሁ የምጠይቀው የመሠረተ ልማት ደረጃቸውን አይደለም፤ በጤና የመኖር መብት ላይ ያለውን ጥበቃና ጥንቃቄ ነው። የሚነግሩኝ ነገር ሁሉ ያስቀናኛል።

ዛሬ ላወራ የፈለኩት ስለ ድምጽ ብክለት ነው። በሰለጠኑት ሀገራት የድምጽ ብክለት እጅግ ትልቅ ጉዳይ ነው፤ በእኛ ሀገር ግን የቅንጦት ነው። ምናልባትም ‹‹ምን ያህል ሥራ ፈት ቢሆን ነው!›› ያሰኝ ይሆናል። የድምጽ እና የአየር ብክለት ግን እንደ ቀላል የሚታዩ አይደሉም። የአየር ብክለት ባናሳካውም ቢያንስ አጀንዳ ስለሆነ እና በተደጋጋሚ ስለሚወራበት ማንም ያውቀዋል። እጅግ ልብ ያልተባለውና የጆሮ ጠላት የሆነው የድምጽ ብክለት ግን በአገራችን አደገኛ ችግር እያመጣ ነው።

የድምጽ ብክለት በሰለጠኑት ሀገራት ከፍተኛ ጥበቃ የሚደረግበት ነው። እያንዳንዱ የምትወጣ ድምጽ መለኪያ አላት፤ ከዚያች ካለፈ ለቃቂው አካል ይጠየቃል። እንኳን ሌላ የተሽከርካሪ ክላክስ መጠን አለው። ከዚያ ካለፈ ይቀጣል፤ መጠን ብቻ አይደለም፤ ክላክስ የሚያደርግባቸው ምክንያቶች ውስን እና የታወቁ ብቻ ናቸው።

በኢትዮጵያ ግን ልብ በሉ! ከፊቱ ያለው ተሽከርካሪ መብራት ይዞት እያየ ከኋላ የመጣው ያለምንም ማቋረጥ ለረጅም ደቂቃ ያንባርቃል። መብራት ይዞት እያየ እንዴት ይሄዳል ብሎ ይሆን? ከፊቱ ያሉ ተሽከርካሪዎች የቆሙበትን ምክንያት እያወቀ አካባቢውን የሚያናውጥ ክላክስ ያስጮሃል።

የሕግ ባለሙያው አብዱ ዓሊጂራ ከጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ ጋር በሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ‹‹ሸገር ካፌ›› ፕሮግራም በአንድ ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲያወሩ ሰምቼ ነበር። አብዱ ሕጎቹን ሲናገር ከወንጀል ሕግ ያልተናነሱ ናቸው። የሚገርመው ግን ከራሳቸው ከአሽከርካሪዎች ጀምሮ እነዚያን ሕጎች አብዛኛው ሕዝብ አያውቅም፤ አብዱ ራሱ ይህን ሲናገር ነበር። ክላክስ የሚደረግበት ምክንያት ተወስኖ የተቀመጠ ነው፤ ከዚያ ውጭ ያደረገ ይቀጣል።

ትልቁ እና አደገኛው ክላክስ አደራረግ ደግሞ ከፊት ላለ እግረኛ የሚደረግ ክላክስ ነው። ክላክስ የሚደረገው ሰውየው ድምፁን ሰምቶ ገለል እንዲል እንጂ ተደነባብሮ እንዲወድቅ አይደለም። ሕጻናት ወይም ከገጠር የመጡ ሰዎች ተደነባብረው ወደ ተሽከርካሪው ራሱ ሊሄዱ ይችላሉ። ‹‹ጺጵ ጺጵ›› የሚል ድምፅ መስጠት ሲገባ፣ ገና ከሩቅ ላለ ሰው ያለምንም ማቋረጥ በረጅሙ አካባቢውን የሚያናውጥ ክላክስ ማድረግ መንገደኛው ተደነባብሮ ምናልባትም ከሌላ ተሽከርካሪ ጋር እንዲጋጭ ያደርጋል።

ሌላው አደገኛ የድምፅ ብክለት ደግሞ የሙዚቃ ነገር ነው። መቼም ስለሙዚቃ ጥቅምና አስፈላጊነት ለማንም ማስረዳት አያስፈልግም። ያም ሆኖ ግን የሰውን ጆሮ ጤና የሚያበላሽ አለቃቀቅ አንድ ሊባል ይገባል። ምግብ ቤቶች ገና በማለዳ በሞንታርቦ የጆሮ ታምቡር የሚበጥስ ሙዚቃ ይከፍታሉ። ደንበኛው የሙዚቃውን ለዛ ከማዳመጥ ይልቅ የውስጡን ጤና ነው የሚያዳምጥ። ከአስተናጋጅ ጋር የሚወራው በከፍተኛ ጩኸት ነው። አብሮን ካለ ጓደኛ ጋር ስናወራ ቆይተን ስንወጣ የጮህንበት ጉሮሯችን ሊዘጋ ሁሉ ይችላል። በማለዳ ምግብ ቤት ውስጥ ጆሮ የሚበጥስ ሙዚቃ መክፈት እስኪ ምንድነው አስፈላጊነቱ? የምር በዚያ ሙዚቃ የሚዝናና አለ? ቢኖር እንኳን ቢያንስ ለአብዛኛው ደህንነት ሲባል ገደብ ሊወጣ እና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

ሌላው የምታዘበው ደግሞ ተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚከፈት ሬዲዮ ነው። አሁንም ስለሬዲዮ አስፈላጊነት ልናወራ አይገባም፤ ዳሩ ግን ጤናን የሚያውክ እና የሚወራውን መስማት እስከሚያስቸግር ድረስ የሚጮህ መሆን የለበትም።

እዚህ ላይ ያለኝን ትዝብት እጥፍ ድርብ የሚያደርገው ደግሞ የመንግሥት ሠራተኞች ማመላለሻ (ፐብሊክ ሰርቪስ) ውስጥ መሆኑ ነው። የመንግሥት ሠራተኛ ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የተማረ ነው። ቢያንስ ዲፕሎማ እና የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ነው። ለአገር ዕድገትና ሥልጣኔ የሚሠራ ነው፤ ዳሩ ግን እንደዚያ ሲጮህ ምንም አይመስላቸውም።

በተለይ ደግሞ የተቀረጸ (ፕሮዳክሽን) ሥራዎች (ማስታወቂያዎች እና የተለያዩ መልዕክቶች ማለት ነው) ሲሆኑ በጣም ነው የሚጮሁት፤ የቀጥታ ሥርጭት ዜናዎችና ፕሮግራሞች ይሻላሉ። ሬዲዮ እንደዚያ እየጮኸ፣ ሰዎች ደግሞ ለመሰማማት ሲሉ በጣም እየጮሁ ያወራሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ሰርቪሱ በድምጽ ይናወጣል። አንዳንድ ደፈር ያሉ ሰዎች ‹‹ኧረ ቀንሰው!›› ሲሉትም አይሰማም። ሁሉም ተስማምቶ ግን ‹‹እየተጎዳን ነው ይቀነስ›› ቢባል አሽከርካሪውም ተጠያቂ ይሆን ነበር።

ችግሩ የአንድ አሽከርካሪ ወይም የአንድ ሬስቶራንት ብቻ አይደለም፤ እንደ አጠቃላይ ያለን ግንዛቤ ደካማ ስለሆነ ነው። የድምፅ ብክለትን እንደ ችግር ስለማናየው ነው። በየመንገዱ ዳር ያላስፈላጊ የሚለቀቁ ድምጾችን የሚቆጣጠር ስለሌለ ነው። ልብስ ቤቶች (ቡቲክ) ሁሉ ሳይቀር በሞንታርቦ ሙዚቃ ይለቀቃል። በተከታታይ ያሉ ቤቶች ሁሉም የየራሳቸውን ሙዚቃ ይለቃሉ፤ አላፊ አግዳሚው ግን የሚሰማው ጩኸቱን እንጂ አንዱንም ሙዚቃ የማጣጣም ዕድል አይኖረውም፤ ምክንያቱም አንዱ ሌላውን እየሸፈነ መረባበሽ ነው።

በነገራችን ላይ በድምፅ ብክለት ላይ የተሠሩ ጥናቶችና መጣጥፎች እንደሚያሳዩት ፈልገን የማንሰማው ድምፅ ሁሉ ‹‹ምቾት የሌለው›› ተብሎ ነው የሚገለጽ። በሌላ በኩል የድምጽ መጠኑም መለኪያ አለው። የድምጽ መለኪያ ዴሲቤል ይባላል፤ ከ60 ዴሲቤል በላይ የሆነ ድምጽ ሁሉ ጎጂ ነው። በዚህ መለኪያ አዲስ አበባ ውስጥ በየመንገዱ የምንሰማውን ድምጽ አስቡት።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን የድምጽ ብክለትን ማንም እንደ ችግርና እንደ ጎጂ አይቶት የሚያውቅ ያለ አይመስልም። ምንም እንኳን እንደ አጠቃላይ የጤና ደህንነት ላይ ያለን ግንዛቤ ደካማ ቢሆንም፣ ጆሯችንን ግን ትርፍ አካል ነው ያስመሰልነው። በነገራችን ላይ ጆሮ የድምፅ መቀበያ የሰውነት ክፍል ይሁን እንጂ ችግሩ ጆሮ ላይ ብቻ የሚቀር አይደለም። ከፍተኛ የሆነ የድምፅ ጫጫታና ጩኸት ሲበዛብን ራሳችንን(ጭንቅላት) የሚያመን ከጆሮ አልፎ ስለሚሄድ ነው። ስለዚህ የድምፅ ብክለት ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል ነው።

ከተማ ነውና የድምጽ ጫጫታ አይኑር ማለት አይቻልም፤ ዳሩ ግን ነባራዊ ሁኔታው ከሚፈጥረው ውጭ ያሉትን እና ሆን ተብሎ ያለአዋቂነት የሚለቀቁ ድምጾችን መቆጣጠር ይቻላል። ገና በማለዳ ምግብ ቤት ውስጥ በሞንታርቦ አካባቢውን ማናወጥ አስገዳጅ አይደለም፣ የትራፊክ መብራት የያዘው ተሽከርካሪ ላይ ያላቋረጠ ክላክስ ማድረግ የሚያስቀጣ መሆን አለበት፣ ተሽከርካሪ ውስጥ ሬዲዮ እስከ ላንቃው መልቀቅ መከልከል አለበት፤ ድምጹ ቀነስ ቢል ምን ችግር አለው?

በአጠቃላይ ጆሮ ከአምስቱ የስሜት ሕዋሳት አንዱ እንጂ ትርፍ የሰውነት ክፍል አይደለምና የድምፅ ብክለት ትኩረት ይሰጠው!

# ዓለም አቀፍ

## ግዙፉ የክሪፕቶከረንሲ ተቋም 3 ነጥብ 1 ቢሊዮን ዶላር እዳ አለበት ተብሏል




በዓለም ሁለተኛው የክሪፕቶከረንሲ የገንዘብ መለዋወጫ 50 የሚሆኑ ዋነኛ አበዳሪዎቹ 3.1 ቢሊዮን ዶላር እዳ እንዳለበት አንድ የፍርድ ቤት ሰነድ አመለከተ። ችግር ላይ የወደቀው የክሪፕቶከረንሲ ተቋም ባለፈው ሳምንት መክሰሩን አሜሪካ ውስጥ ያሳወቀ ሲሆን፣ ስማቸውን ያልጠቀሳቸው የ10 ዋነኛ አበዳሪዎቹ 1.45 ቢሊዮን ዶላር እዳ እንዳለበት ገልጿል።

በዚህም ሳቢያ የኤፍቲኤክስ (FTX) የበላይ ኃላፊ ሳም ባንክማን-ፍራይድ ከተቋሙ መሪነት በፈቃዱ እንዲወርድ አስገድዶታል። ይህ በዓለም ሁለተኛው ትልቁ የክሪፕቶከረንሲ የገንዘብ መለዋወጫ የሆነው ኤፍቲኤክስ (FTX) ክስረት፣ ችግር ውስጥ የሚገኘውን የክሪፕቶ ገበያን አስተማማኝነት የበለጠ አናግቶታል።

ኤፍቲኤክስ ቀደም ሲል ይፋ ባደረገው የኪሳራ ማሳወቂያ ላይ የገጠመውን ውድቅት ተከትሎ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች እና የንግድ ተቋማት ገንዘባቸውን ሊጠይቁ ይችላሉ ብሏል። ባለፈው ቅዳሜ ኤፍቲኤክስ እንዳሳወቀው በዓለም ዙሪያ ያሉትን ሃብቶች ለሽያጭ ለማዘጋጀት ወይም አንዳንዶቹን የንግድ ተቋማት መልሶ ለማደራጀት የሚያስችል ግምገማ ማድረግ ጀምሯል።

የክሪፕቶከረንሲው ተቋም የኪሳራ ጉዳይን ለመመልከት ነገ ማክሰኞ ፍርድ ቤት ይሰየማል ተብሎ ይጠበቃል። ይህ የኪሳራ ጉዳይ በፍርድ ቤት ሂደት ውስጥ ካላፈ በኋላ በዝውውሩ ውስጥ ገንዘባቸውን ካፈሰሱት ሰዎች መካከል ምን ያህሉ ሀብታቸውን መልሰው ያገኛሉ የሚለው እስካሁን ግልጽ አይደለም። ነገር ግን የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያስጠነቅቁት የሚያገኙ ከሆነ ከአጠቃላይ ገንዘባቸው በጣም ትንሹን ሊሆን ይችላል።

ባለፈው ሳምንት አዲሱ የኤፍቲኤክስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ጆን ሬይ የከሰረው የክሪፕቶ ድርጅት ሲመራበት የነበረውን መንገድ “እንዲህ አይነት ድርጅት በመምራት ሂደት ውስጥ አጠቃላይ የቁጥጥር ውድቀት አጋጥሞኝ አያውቅም” በማለት ክፉኛ ተችተዋል።

በገዛ ፈቃዱ ከኃላፊነቱ የለቀቁትን ባንክማን-ፍሬይድን የተኩት ሬይ ጨምረውም በተቋሙ ውስጥ “እምነት የሚጣልበት የገንዘብ ዝውውር መረጃ ሙሉ ለሙሉ የለም” ሲሉም ተችተዋል። የቀድሞው ኃላፊም ባንክማን-ፍራይድ ለቪክስ የዜና ድረ ገጽ የገንዘብ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሳኔዎች ከእሳቸው ቁጥጥር ውጪ መሆናቸውን በመጥቀስ ኤፍቲኤክስ ኪሳራ በማወጁ እንደሚጸጸቱ ተናግረዋል። በተጨማሪም የገንዘብ ተቋማት ተቆጣጣሪዎች የነበራቸውን ቸልተኝነት ተችቷል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## የደቡብ አፍሪካ ፍርድ ቤት የጸረ አፓርታይድ ታጋዩን የገደለው ቀኝ አክራሪ እንዲፈታ ወሰነ



የደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸረ አፓርታይድ ነጻነት ታጋይ የሆነውን ክሪስ ሃኒን የገደለው የቀኝ አክራሪ ታጣቂ ከእስር እንዲፈታ ወሰነ።

በበርካታ ደቡብ አፍሪካውያን በተለይም ወጣቶች ዘንድ እንደ ጀግና የሚታየው ክሪስ ሃኒ የተገደለው በአውሮፓውያኑ 1993 ነበር። ጃንሰስ ዋሉስ “ከበድ ያለ ወንጀል” ቢፈጽምም” ነገር ግን እንደ ሌሎች እስረኞች በአመክሮ የመውጣት መብት እንዳለው ፍርድ ቤቱ ወስኗል።

ይህንን ውሳኔም የክሪስ ሃኒ ባለቤት ሊምፖ “በእውነት ዲያብሎሳዊ” ነው ስትል አውግዛዋለች። ለሦስት አስርተ ዓመታት በእስር የቆየው የ69 ዓመቱ ዋሉስ ነጻነቱን ለማግኘት ያደረጋቸውን ሙከራዎች እሷም ትሁን የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በብርቱ ሲቃወሟቸው ነበር። ዋሉስ ክሪስ ሃኒን የገደለው የደቡብ አፍሪካ አናሳና ጨቋኝ አገዛዝ ተገርስሶ ወደ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር የሚደረገው ሙከራ እንዳይሳካ በሚል ነበር ።

ዋናው ዳኛ ሬይ ዞንዶ የሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቱን ወክለው በሰጡት ብይን ዋሉስ ክሪስ ሃኒን በጭካኔ ከገደለ በኋላ ሀገሪቷ ወደ እርስ በርስ ጦርነት ለመግባት ተቃርባ ነበር ብለዋል። ነገር ግን የፍትሕ ሚኒስትሩ ሮናልድ ላሞላ በአመክሮ እንዳይወጣ መወሰናቸው “ምክንያታዊነት የጎደለው ነው” እና በ10 ቀናት ውስጥ ሊፈታ ይገባል ብለዋል ዋና ዳኛው።

አክለውም “ሁሉም ሰው በሕግ ፊት እኩል ነው የሚለው መርሆ አፓርታይድን ለተዋጉት ብቻ ሳይሆን በንቃት ለሚደግፉት ጭምር ነው” ሲሉ መናገራቸውን የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። የፍትሕ አገልግሎት ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ክሪስፒን ፒሪ “ፍርድ ቤቱ ወስኗል እናም ተግባራዊ ማድረግ አለብን” ማለታቸውን አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የዜና ወኪል ዘግቧል.

ክሪስ ሃኒ የደቡብ አፍሪካ ኮሚዩኒስት ፓርቲ (ኤስኤሲፒ) መሪ እና በደቡብ አፍሪካ ለነጻነት የታገለው እና ስልጣን የተቆጣጠረው የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ወታደራዊ ክንፍ ከፍተኛ አመራር ነበር። ክሪስ ሃኒን በመግደል ተባባሪ የነበረው ክሊቭ ደርቢ ሌዊስ በአውሮፓውያኑ 2015 መፈታቱ ይታወሳል።

ክሊቭ ክሪስ ሃኒን የሚገደልበትን ሽጉጥ ለዋሉስ በመስጠትም ወንጀል ነበር የተፈረደበት። ግለሰቡ በተፈታ በዓመቱ በ80 ዓመቱ ሕይወቱ አልፏል። ዋሉስ የፖሊሽ ስደተኛ ሲሆን በአውሮፓውያኑ 2017 ደቡብ አፍሪካ የሰጠችውን ዜግነት ነጥቃዋለች። አንዳንዶቹም ከሃገር እንዲባረር ጠይቀዋል።

የደቡብ አፍሪካ ኮሚዩኒስት ፓርቲ የክሪስ ሃኒ ግድያ “በቤተሰቡ፣ በፓርቲው እና በሠራተኛው መደብ ላይ ከፍተኛ ክፍተትን የፈጠረ ነው” ብሏል።“ብያኔው የነበረው ቁስል ላይ እንዲያመረቅዝ የሚያደርግ ነው ብሏል። ዋሉስ በእስር ቤትም ቆይታው ለወጣት ፖላንድ አክራሪና ጭፍን ብሔርተኞች እና ፋሺስቶች ምልክት መሆን ችሏል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የአዲስ አበባ ጤና ስፖርት ማህበራት ውድድር በመርካቶ አሸናፊነት ተጠናቀቀ

**ቦጋለ አበበ**

ከባለፈው ዓመት ነሐሴ 1 ጀምሮ በቢሾፍቱ ከተማ ሲካሄድ የቆየው የጤና ስፖርት ማህበራት ውድድር ፍጻሜ አግኝቷል። ከ35፣ ከ40 እና ከ50 ዓመት በላይ ምድብ የዙርና የጥሎ ማለፍ ጨዋታዎች ተደርገው ላሸነፉ ቡድኖች እውቅና እና የዋንጫ ሽልማት በመስጠት ውድድሩ ሲጠናቀቅ የመርካቶ አካባቢ ጤና ስፖርት ማህበር አጠቃላይ አሸናፊ መሆን ችሏል።

በቢሾፍቱ ስታድዬም ከ50 ዓመት በላይ በተደረገ የፍጻሜ ጨዋታ መርካቶ ጤና ስፖርት ማህበር የቢሾፍቱ አቻውን በመለያ ምት በመርታት ቻምፒዮን ሆኗል። በኦሊምፒክ ሜዳ በተደረገ ከ40 ዓመት በላይ መርሃ ግብርም መርካቶ ሳሪስን በማሸነፍ የምድቡ ባለ ድል ሆኗል።

ከ35 ዓመት በታች የተካሄደውን የዙር ጨዋታ ቢሾፍቱ ከተማ ጤና ስፖርት ማህበር በበላይነት አጠናቆ የዋንጫ ባለቤት ሆኗል። ከሦስት ወራት ለበለጠ ጊዜ በቢሾፍቱ የተለያዩ ስታድዬሞች በተከናወኑ ጨዋታዎች በኮከብ ተጨዋችነትና ግብ አስቆጣሪነት ብሎም በኮከብ አሰልጣኝነት የተመረጡ ተሳታፊዎችም እንደ ውጤታቸው የተለያዩ የማበረታቻ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል።



የመርካቶ አካባቢ የጤና ስፖርት ቡድን አጠቃላይ አሸናፊ በመሆን ዋንጫ ወስዷል፣

ዓመታዊ ውድድሩ በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ የኢትዮጵያ ጤና ስፖርት ማህበርን ከመመስረት በተጨማሪ የውድድሮችን ቁጥር ማሳደግ ላይ ትኩረት እንደሚሰጥ የአዲስ አበባ ጤና ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት ተፈራ ደምበል ተናግረዋል።

ከውድድሩ አሸናፊዎች ባለፈ በምስጉንነታቸው ለተመረጡ ማህበራት፣ በትክክለኛ ዕድሜ ተሳታፊዎችን ላቀረቡ ቡድኖችና ለማህበሩ ፍሬያማነት ለተጉ በጎ ፍቃደኞች የቢሾፍቱ ከተማ የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች እንግዶች የእውቅና ሰርተፊኬትና ሽልማት በመስጠት ዓመታዊ ውድድሩ ተጠናቋል።

ከ20 በላይ የጤና ቡድኖች በሦስት የዕድሜ ካታጎሪ ተከፍለው ላለፉት አስራ ሦስት ሳምንታት ሲወዳደሩ የቆዩበት ይህ የስፖርት መድረክ በየአመቱ ኅብረተሰቡ ስፖርት በመስራት ጤናውን እንዲጠብቅ ከማድረጉም ባሻገር በተጨዋቾች ዘንድ ቅርርብን በመፍጠር ወንድማማችነትን እና ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር ከመፍጠር አኳያ ሰፊ ድርሻ እንዳለው ተጠቁሟል።

የዘንድሮ ውድድር የአዲስ አበባ ጤና ቡድን አመራሮች፣ የውድድር ኮሚሽነሮች እና አልቢትሮች ከሌላው ጊዜ አንፃር ጨዋታዎቹን በጥሩ ሁኔታ በመምራት እንዳጠናቀቁም ከማህበሩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በ1986 ዓ.ም በሁለት ቡድኖች የተጀመረው የአዲስ አበባ ጤና ስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ ዛሬ ላይ አርባ ሁለት ማሕበራትን እያሳተፈ ይገኛል። እነዚህ ማሕበራት በየአካባቢው ከዚህ ቀደም በስፖርቱ ውስጥ ያለፉ ግለሰቦችን ያካተቱ ሲሆን ቢሾፍቱ ላይ የሚያካሂዱትን ዓመታዊ ውድድርም በሦስት የዕድሜ ካታጎሪ ተከፍለው ያካሂዳሉ። ከ35 ዓመት በታች፣ ከ40 ዓመት በታችና ከ50 ዓመት በላይ ዕድሜ ላይ የሚገኙ የማሕበራቱ አባላት ውድድሮችን ያካሂዳሉ።

ሁሉም ውድድሮች የእግር ኳስን ሕግና ደንብ መሠረት አድርገው የሚካሄዱ ሲሆን፣ ከአስራ ሦስት ሳምንታት በላይ በሚፈጀው ፉክክር 208 ጨዋታዎች ይከናወናሉ። በዘንድሮው ውድድር አራት አዳዲስ ማሕበራት የተካተቱ ሲሆን፣ በመክፈቻው ዕለት ሃያ ያህል ጨዋታዎች በቢሾፍቱ ሰባት የተለያዩ ሜዳዎች ተከናውነዋል። እንደ አጠቃላይ ከሃያ ሺ በላይ ተመልካቾችም ይህን ውድድር ይከታተላሉ።

ከአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## በተቋሙ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከስሩ ለማድረቅ የተዘረጉ አሠራሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች

**ሶሎሞን በየነ**

በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ለውጥ እንዲመጣ ካደረጉ አስገዳጅ ምክንያቶች አንዱ በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረው ሙስናና ብልሹ አሠራር ነው። ይህንን የተረዳው የለውጡ ኃይልም በሀገሪቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመቅረፍ በርካታ የፖሊሲ ማዕቀፎች፣ የሪፎርም ማሻሻያዎች፣ የሕግ፣ የአሠራርና አደረጃጀት ማስተካከያ እርምጃዎች ወስዷል። እየወሰደም ይገኛል። ከሰሞኑም መንግሥት እየተንሠራፋ የመጣውን ሙስናን ለመቀነስ ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ አዋቅሯል። ተቋማትም በበኩላቸው የተደረጉ የሪፎርም ሥራዎችን ተቀብለው ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመቅረፍ እየተጉ ይገኛሉ።

ከዚህ አንጻር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት ቢሮ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት እያከናወነ ያለውን ሥራ በተመለከተ ከተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ ጋር እንደሚከተለው ቆይታ አድርገናል።

እንደዶክተር ገበየሁ ገለጻ፤ ቀደም ባለው ጊዜ በተቋሙ እምብዛም በሥነምግባር ረገድ የሚነሳ የጎላ ችግር አልነበረም። የዕቃ አቅርቦቱና ጥራቱም የተሻለ ነበር። ሆኖም ሀገሪቱ ከውጭ የምታስገባቸውን ምርቶች በአገር ውስጥ ምርት በመተካት የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት ታስቦ ሜቴክ በ2002 ዓ.ም ተቋቋመ። ይህ ድርጅት መቋቋሙን ተከትሎ ተቋማት ከውጭ ዕቃዎች እንዳያስገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተቀምጦ ነበር። ስለዚህ ሜቴክ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን እያመረተ ለተቋማት ያቀርብ ጀመረ። ሆኖም ድርጅቱ ዕቃዎችን ሊያቀርብ ኮንትራት ተፈራርሞ ቅድመ ክፍያ ይወስዳል ነገር ግን በውሉ መሠረት በጊዜ ማቅረብ ላይ በጣም ከፍተኛ ውስንነቶች ነበሩበት። በዚህም ዕቃውን ሳያቀርብ ከፍተኛ ካፒታል ይዞ ይቀመጣል። እንዲሁም የሚቀርቡ ዕቃዎችም የጥራት መጓደል ነበረባቸው። በዚህ ምክንያት ተቋሙ ከ2002 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ከፍተኛ የሆነ የዕቃ እጥረት ችግሮች ነበሩበት። ይህንን ተከትሎ ብልሹ



ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ፤

ሥነምግባር ያለባቸው ሠራተኞች የምትቀርበውን ውስን ዕቃ ያልተገባ ጥቅማጥቅም በመቀበል ከሕግና ከአሠራር ውጪ ሲያውሉ ጎልቶ ይታይ ጀመር። በጥቅሉ የሥነምግባር ግድፈቱ ጎልቶ የተፈጠረው ከዚህ አኳያ ነው።

አሁን ላይ ይህንን ችግር ለመፍታት ፈርጀ ብዙ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። አንደኛው ፖለቲካዊ ለውጡ ከመምጣቱ አስቀድሞ ተመዝግበው ኃይል በመጠባበቅ ላይ ያሉ ደንበኞች ነበሩ። እነዚህን ደንበኞች ቶሎ ቶሎ ማስተናገድና ለጥያቄያቸው ምላሽ መስጠት የሥነምግባር ችግሩን ይፈታዋል። ከዚህ አንጻር ተመዝግበው ኃይል የሚጠባበቁ ደንበኞችን ኃይል እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። በዚህም ተመዝግበው ኃይል የሚጠባበቁ 12 ሺ ደንበኞችን እስከ ታኅሳስ 30/2015 ዓ.ም ድረስ እናጠናቅቃለን። ይህ ሲጠናቀቅ አንድ ኃይል የሚገናኝበት የጊዜ መለኪያ ወይም መስፈርት አለ። ወደዛ ስታንዳርድ ይገባል። ይህም በወረፋ ምክንያት የሚመጣውን ብልሹ አሠራር ለመቆጣጠር ያስችላል። ሌላው ደግሞ ይህ ሲጠናቀቅ ወደ ስታንዳርድ ስለሚገባ ወይም ደግሞ ተመዝግቦ ኃይል በመጠባበቅ ላይ ያለው የመዲናዋ ነዋሪ ቁጥር እያነሰ ስለሚመጣ የቁጥጥርና የክትትል ሥራው አመቺ እንደሚሆን ይናገራሉ።

70 በመቶ አዲስ ኃይል ከማገናኘትና ግምት ጋር በተያያዘ የሥነምግባር ችግሩ ጎልቶ እንደሚስተዋል ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመው፤ የሥነምግባር ግድፈቱን ለመቆጣጠር ሌላው እንደስትራቴጂ የተወሰደው ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶና ተናቦ መሥራት ነው። ስለዚህ ባለው አደረጃጀት ከደህንነት፣ ከፖሊስ እንዲሁም ከተጠሪ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው። በቅንጅት በተደረገው የቁጥጥር ሥራም የተጋለጡ ሠራተኞች አሉ።

እንዲሁም ቀደም ሲል በነበረው አሠራር ደንበኛው ኃይል ለማግኘት መቼ፣ የትና ማነው? ያመለከተው የሚለው አይታወቅም ነበር። በዚህም «በከክልህ እከከኝ» አንዱ ያለወረፋው ኃይል የሚያገኝበት ሌላኛው ለረጅም ጊዜ ተመዝግቦ ኃይል ሳያገኝ የሚጉላለበት ሁኔታ ነበር። አሁን ላይ ይሄን ችግር የሚቀርፍ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተዘርግቷል። ስለዚህ አጠቃላይ ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት መቼ አመልክተው መቼ ቆጣሪ ይገባላቸዋል የሚለው ሥርዓቱ ላይ ተመዝግቦ ስለተቀመጠ ማንም አካል ብድግ ብሎ ሊቀንሰው ሊጨምረው አይችልም። ስለዚህ ፋይልህ ጠፍቷል በሚል ወረፋ ማዛባት ወ.ዘ.ተ አይቻልም። ችግሩ በሲስተም ተመልሷል። በዚህም ዕቃ እያለ በወቅቱ ያለማስተናገድ የሥነ ምግባር ግድፈቶች የተስተዋለባቸው ሠራተኞች ላይ እርምጃ ተወስዷል።

ከዚህ ባሻገር የሥነምግባር ክበባት በ30 የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት አሉ። በነዚህ ማዕከላት የሥነ ምግባርና ጸረሙስና ክበባት ተቋቁመዋል። በየማዕከላቱም የደንበኞች ፎረም በወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል። በዚህ ፎረምም ደንበኞች በየአካባቢያቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግር የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ፊት ለፊት ውይይት ይደረጋል። እንዲሁም በዲስትሪክት ደግሞ በሦስት ወር አንዴ የኢንዱስትሪ ደንበኞች ፎረም ይደረጋል። በዚህም በተመሳሳይ ከደንበኞች ግብረ መልሶችን እናገኛለን። ሌላው ደግሞ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመዋጋት በዋናው ቢሮ የሥነ ምግባርና ጸረሙስና ዳይሬክቶሬት አለ። ዳይሬክተሩ በራሱ የሚያጠናቸው ጥናቶች አሉ። ጥቆማ የሚቀበልበትም ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ሥርዓት ተዘርግቷል። ስለዚህ በነዚህ አደረጃጀቶች ተጠያቂ መሆን የሚገባው ተጠያቂ እየተደረገ የቁጥጥር ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በነዚህ ሁሉ አደረጃጀቶች መቆጣጠርና ማስተካከል ሳይቻል ቀርቶ በሥነ ምግባር ብልሹነት ተዘፍቆ የተገኘን አካል የተጠያቂነት ሥርዓት ማስፈን ያስፈልጋል። በዚህም ሌብነትን ጨምሮ ደንበኞችን በሥርዓቱ አለማስተናገድ፣ የሥራ ሰዓት መሸራረፍ፣ በሥራ ቦታ አለመገኘት… ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ የሥነ ምግባር ብልሹነት ተዘፍቀው የተገኙ ሠራተኞች ላይ የማስተማሪያ እርምጃ ተወስዷል። ለአብነት ባለፈው በጀት ዓመት 121 የሚሆኑ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ የማስተማሪያ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ 16ቱ ከሥራ የተሰናበቱ ናቸው። እርምጃ ከተወሰደባቸው ውስጥ ደግሞ 36ቱ አመራሮች ናቸው። በዚህኛው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ደግሞ 10 ሠራተኞች ከሥራ ተሰናብተዋል። ይህም የሚያሳየው ምህረት የለሽ እርምጃ እየተወሰደ የሥነምግባርና ጸረሙስና ግድፈቱን ለማስተካከል እርብርብ እየተደረገ መሆኑን ነው።

ሆኖም የሥነ ምግባር ግድፈት ያለባቸው ሠራተኞች ላይ እርምጃ ለመውሰድ የደንበኞች ተሳትፎ ወሳኝ ነው። እስካሁን የተወሰዱት እርምጃዎች ያለደንበኞች ተሳትፎ የተወሰዱ አይደሉም። ምክንያቱም ያለደንበኞች ተጨባጭ ጥቆማና ምስክርነት አንድን ሠራተኛ ተጠርጥረሃል በሚል እርምጃ መውሰድ አይቻልም። ምክንያቱም ሕጉም አሠራሩም አይፈቅድም። በመሆኑም ከኅብረተሰቡ አይንና ጆሮ የሚደበቅ ወይም የሚሰወር ስለሌለ እርምጃው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ደንበኞች የተሠሩ ወንጀሎችን በድምጽ በመቅረጽ፣ በአካል ቀርቦ ሪፖርት በማድረግ፣ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመመስከር፣ በአካል ተቋሙ ጋር ቀርቦ በመጠቆምና ማመልከቻ በማስገባት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከተቋሙ ጋር እጅ ለጅ ተያይዞ አጥብቆ ሊዋጋ እንደሚገባ ዋና ሥራ አስፈጻሚው አሳስበዋል።

**አድራሻ**
ኢ.ሜል / E-Mail= aacaeucommunication30csc@gmail.com
ፌስቡክ/ Facebook= https://www.facebook.com/AAREUofficial
ቲዊተር/ Twitter = https://twitter.com/AARE_Utility
ቴሌግራም/ Telegram = https://t.me/addisababaelectricutility
ስልክ/ TELE = 011-636-60-00
= 0116367133

የአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ